የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት

# የአፋር ክልል ነጋሪት ጋዜጣ

# AFAR REGION NEGARIT GAZETA

**OF THE AFAR NATIONAL REGIONAL STATE**

| ስምንተኛ ዓመት<br>ሠመራ ሰኔ ፩ ቀን ፲፱፻፺፭ | በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት<br>ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ | 8th Year<br>SEMERA – May, 2003 |
|---|---|---|

## ማውጫ


አዋጅ ቁጥር ፳፪/፲፱፻፺፭ ዓ.ም

የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ፖሊስ ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፳፪/፲፱፻፺፭ ዓ.ም ................................ ገጽ ፩


## CONTENTS


Proclamation No. 22/2003

''Afar National Regional State Police Commission Establishment Proclamation No. 22/2003'' ..... Page 1


### የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ፖሊስ ኮሚሽን አደረጃጀትንና አስተዳደርን ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር ፳፪/፲፱፻፺፭ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ "ሕገ መንግሥት"ና በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት "ሕገ መንግሥት" እንዲሁም ሕገ መንግሥቱን መሠረት አድርገው ለሚወጡ ሕጎች ብቻ ተገዢ የሆነና በፖሊሳዊ ሙያ የተሟላ ሥልጠናና ብቃት ያለው ለሕዝብ አገልጋይ የሆነ፣ ሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶችን የሚያከብርና የሚያስከብር፣ የሕዝብን ሰላምና ደህንነት የሚያረጋግጥ የተጠናከረ የሲቪል ፖሊስ ተቋም እንዲኖር ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፣

በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት ተሻሽሎ በወጣው ሕገ መንግሥት አንቀጽ "፵፯" ቁጥር ፪ "ለ" እና "ሰ" መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

#### ክፍል አንድ
#### ጠቅላላ ድንጋጌዎች

፩· <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ፖሊስ ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፳፪/፲፱፻፺፭ ዓ.ም ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪· <u>ትርጓሜ</u>

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፣

፩· "ፖሊስ" ማለት መሠረታዊ የሆነ የፖሊስ ሙያ ሥልጠና ተሰጥቶት በኮሚሽኑ ተቀጥሮ የሚሰራ የአፋር ክልል ፖሊስ ኮሚሽን አባል ነው።

### THE AFAR NATIONAL/REGIONAL STATE POLICE COMMISSION ESTABLISHMENT PROCLAMATION NO. 22/2003 DEFINIITION OF THE ORGANIZATION AND ADMINISTRATION OF THE AFAR NATIONAL REGIONAL STATE POLICE COMMISSION

WHEREAS, it has become necessary to have a well-organized and strong Civil Police Institution which is faithful to the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and to the Constitution of the Afar National/ Regional State, and respectful to the laws enacted in accordance with the Constitution, equipped with adequate training required for his profession, and that serves the public, respects, ensures the observance of human and democratic rights, and maintains peace and welfare of the public;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 47(b) and (g) of the amended Constitution of the Afar National Regional State Council, it is hereby proclaimed as follows.

#### PART ONE
#### *General Provisions*

1. *Short Title*

This Proclamation may be cited as the ''Afar National Regional State Police Commission Establishment Proclamation No. 22/2003''.

2. *Definitions*

In this Proclamation unless the context requires otherwise:

1) ''Police Officer'' means a member of the Afar Regional Police Commission who has received basic training in the Police profession and is employed by the Commission;


| |
|---|
| ያንዱ ዋጋ<br>Unit Price 9.30 |

፪· "ጉባኤ" ማለት የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ፖሊስ ኮሚሽነሮች እና የዞን ፖሊስ ዴስክ ኃላፊዎች ጉባኤ ማለት ነው።

፫· "የማስተባበሪያ ቢሮ ኃላፊ" ወይም "ማስተባበሪያ ቢሮ" ማለት እንደ ቅደም ተከተሉ የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የአስተዳደርና ፍትሕ ጉዳይ ማስተባበሪያ ቢሮ ኃላፊ ወይም የአፋር ብሔ/ክል/መን/የአስተዳደርና ፍትህ ጉዳይ ማስተባበሪያ ቢሮ ነው።።

፫· ስያሜ

የአፋር ክልል ፖሊስ ኮሚሽን "አፋር ክልል ፖሊስ" (አፋ·ክ·ፖ) ተብሎ ይጠራል።

ክፍል ሁለት

ስለ አፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ፖሊስ ኮሚሽን መቋቋም

፬· መቋቋም

፩· የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ፖሊስ ኮሚሽን (ከዚህ በኋላ "ኮሚሽን" በመባል የሚታወቅ) በዚሁ አዋጅ ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው በስሩ የተለያዩ የሥራ ዘርፎችን የሚመራ የክልሉ አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።

፪· ኮሚሽኑ በሕግና በሙያ የሚኖረው ነፃነት እንደተጠበቀ ሆኖ ተጠሪነቱ ለአስተዳደርና ፍትሕ ማስተባበሪያ ቢሮ ኃላፊ ይሆናል።

፭· የኮሚሽኑ ዋና መሥሪያ ቤት

፩· የኮሚሽኑ ቢሮ ሰመራ ከተማ ይሆናል፣

፪· ኮሚሽኑ የክልሉን መንግሥት መዋቅር ተከትሎ የዞን ፖሊስ ዴስክና የወረዳ ፖሊስ ጽ/ቤቶች ይኖሩታል፣ እንዲሁም አስፈላጊ ሲሆን በክልሉ በማናቸውም ሥፍራ የወረዳ ንዑስ ፖሊስ ጣቢያዎች ያቋቁማል።

፫· ኮሚሽኑ መምሪያዎች፣ አገልግሎቶች፣ ዋና ክፍሎችና ሌሎች ለኮሚሽኑ የተሰጡ ሥልጣንና ተግባራት የሚያከናውኑ የመሥሪያ ቤቱ አካላትን ማቋቋም ይችላል።

፮· የኮሚሽኑ ዓላማ

የኮሚሽኑ ዓላማ የሀገሪቱን ሕገ መንግሥትና የክልሉን ሕገ መንግሥት እንዲሁም ሌሎች ሕጎች በማክበርና በማስከበር የሕዝቡን ተሳትፎ መሠረት በማድረግ ወንጀልን በመከላከል፣ የሕዝቡን ሠላማዊ ኑሮና ፀጥታ ማስጠበቅ ነው።

፯· የኮሚሽኑ ሥልጣንና ተግባር

ኮሚሽኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል፣

፩· በክልል ፍርድ ቤቶች ሥልጣን ሥር የሚወድቁ ወንጀሎችን ይከላከላል፣ መርምሮ ለሕግ ያቀርባል።

፪· የፌደራልና የክልሉን ሕገ መንግሥት በመጣስ ሥርዓቱን አደጋ ላይ ሊጥሉ የሚችሉ ማናቸውንም ፀረ ሰላም ፣ ፀረ ዲሞክራሲና ፀረ ልማት እንቅስቃሴዎችን ይከላከላል፣ ሆኖም ከክልሉ አቅም በላይ የሆነ የፀጥታ መደፍረስ ሲያጋጥም የፌደራሉን መንግሥት እገዛና ድጋፍ እንዲጠየቅ ለክልሉ መንግሥት መረጃ ያቀርባል፣

፫· በተደራጀ መልክ የሚፈፀም የፀጥታ ማደፍረስ፣ የሽፍትነት፣ የአሸባሪነት፣ የአደገኛ ዕፅ ዝውውርና ሥርጭትን ይከላከላል፣ ተፈፅሞም ሲገኝ መርምሮ ለሕግ ያቀርባል።

፬· በክልሉ ጥቅሞችና ተቋሞች ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎችን ይከላከላል፣ መርምሮ ለሕግ ያቀርባል።

፭· የክልሉን አጎራባች አገሮች ጠረፍ ደህንነት፣ በክልሉ ውስጥ ያሉ የአየር ማረፊያዎችን፣ የባቡር መስመሮችን፣ ተርሚናሎችን ፣ የማዕድን ማውጫ ቦታዎችን እና ሌሎች ዋና ዋና የፌደራል መንግሥትና የክልል መንግሥት ተቋሞችን ከፌደራሉ ፖሊስ ጋር በመተባበር ይጠብቃል፣

፮· ለከፍተኛ የክልሉ መንግሥት ባለሥልጣናትና ወደ ክልሉ ለሚመጡ የፌደራሉ ከፍተኛ ባለሥልጣኖች እንዲሁም ለውጭ አገር እንግዶች ጥበቃ ያደርጋል፣

፯· በፍርድ ቤት የሚሰጠውን ትዕዛዝ ወይም ውሳኔ ይፈጽማል፣

፰· የወንጀል ምርመራን በተመለከተ የክልሉ ዓቃቤ ሕግ የሚሰጠውን ትዕዛዝ ይፈጽማል፣

2) "Council" means the Council of the Afar National Regional State Police Commissioners and the Zonal Police Desk Officials;

3) "Official of the Coordinating Bureau" or "Coordinating Bureau" means the Afar National Regional State Administration and Justice Affair Coordinating Bureau Official or the Afar National Regional State Administration and Justice Affair Coordinating Bureau, respectively.

3. *Nomenclature*

The Afar Region Police Commission shall be called the 'Afar Region Police".

PART TWO

*Establishment of the Afar National Regional State Police Commission*

4. *Establishment*

1) The Afar National Regional State Police Commission (hereinafter "the Commission") is hereby established as a Regional Organ having its own legal personality, and directing various work-disciplines.

2) Without prejudice to its legal and professional independence, the Commission shall be accountable to the Administration and Justice coordinating Bureau Official.

5. *Head Office*

1) The Head Office of the Commission shall be in Semera Town.

2) Pursuant to the structure of the Regional State, the Commission shall have the Zonal Police Desk and District Police Offices. In addition, where necessary, the District sub-Police Stations shall be established anywhere in the Region.

3) The Commission may establish Departments, Services, Main Sections, and other organs that carryout the powers and functions of the Commission.

6. *Objective of the Commission*

The objective of the Commission is to maintain peace and security of the Public by complying to, and enforcing the Country's and the Region's Constitution and other laws of the country, and by preventing crime through participation of the people.

7. *Powers and Functions of the Commission*

The Commission shall have the following powers and functions:

1) prevent and investigate crimes that fall under the jurisdiction of Region's courts;

2) prevent any activities in violation of the Federal and Regional Constitution; however, if the violation is over-and -above the Region's control, to request the Federal State's alliance, it offers information to the Regional State;

3) prevent violence against public peace, hooliganism, terrorism, trafficking in and transferring of drugs; and if committed, investigate and bring it before the law.

4) prevent crimes against the interests and institutions of the Region;

5) safeguard the security of the Region's borders, airports, railway lines and terminals, mining areas, and other vital institutions of the Federal and Regional State in collaboration with the Federal Police.

6) give security protection to higher officials of the Regional state, to higher officials of the Federal State and dignitaries of foreign countries;

7) execute orders and decisions of courts;

8) execute orders issued by the Regional Public Prosecutor with regard to investigation of crimes;

፱· የክልሉ ፖሊስ ኮሚሽን ከፌደራሉ ፖሊስ ኮሚሽን ጋር በሚኖረው የሥራ ግንኙነት ከወንጀል ነፃ የመሆን ማስረጃ ይሰጣል።

፲· የኮሚሽኑን አደረጃጀት፣ አወቃቀር፣ አሰራርና አቅም ግንባታ በሚመለከት ጥናቶች ያደርጋል። እንዲሁም የወንጀል መከላከልና ምርመራ ሥራዎችን ለማጎልበትና የክልሉን ፖሊስ ሙያ ብቃትና አገልግሎት በሀገር አቀፍ ደረጃ ተመሳሳይነት ያለው ደረጃውን የጠበቀ እንዲሆን ለማድረግ ያጠና፣ በፌደራል ፖሊስ ለሚደረገው ጥናት ትብብር ያደርጋል።

፲፩· በክልል ደረጃ የወንጀል አፈፃፀም፣ የትራፊክ አደጋ መረጃዎችን እና ስታትስቲክሶችን ያሰባስባል፣ ሰብስቦ ያጠናቀረውን መረጃ በመጭመቅ የክልሉን የወንጀል አፈፃፀም ደረጃ ለክልሉ መንግሥትና ለፌደራሉ ፖሊስ ይገልፃል።

፲፪· ከሌሎች ክልል ፖሊስና የፀጥታ አካላት ጋር የመረጃ ልውውጥና የጋራ ኮሚቴያዊ የሥራ ቅንጅት ያደርጋል።

፲፫· የፌደራሉ ፖሊስ በሚሰጠው የአቅም ግንባታ ሥልጠና የሙያ፣ የቴክኒክና የምክር አገልግሎት ድጋፍ ተጠቃሚ ይሆናል።

፲፬· በፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፫፻፲፫/፲፱፻፺፭ ዓ.ም ክፍል ሁለት አንቀጽ "፯" ንዑስ ቁጥር ፲፭ መሠረት በፌደራሉ ፖሊስ በኩል አስፈላጊ ሆኖ ውክልና ሲሰጠው ይቀበላል፣

፲፭· አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ለሌሎች አካላት ወይም ለሲቪል የመንግሥት ሠራተኞች የተወሰኑ ሥራዎችን ለማከናወን የሚያስችል ሥልጣን በውክልና ሊሰጥ ይችላል፣

፲፮· የዞንና የወረዳ ፖሊስ ጽ/ቤቶችን ያደራጃል የሥራ እንቅስቃሴያቸውን በመከታተል ይመራል፣ የክልሉን ፖሊስ ማሰልጠኛ ትምህርት ቤት ያቋቁማል፣ ያስተዳድራል ፣

፲፯· የፖሊሱን የሙያ ብቃት ለማሳደግ፣ በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ሀገር የስልጠና ዕድሎች፣ መመዘኛውን የሚያሟሉ የፖሊስ አመራሮችና አባሎች እንዲሳተፉ ያደርጋል።

፲፰· ከፌደራል እና ከክልል ፖሊስ ኮሚሽኖች ጋር ግንኙነት በመፍጠር የመረጃ ልውውጥ ያደርጋል፣

፲፱· ውል ይዋዋላል፣ የንብረት ባለቤት ይሆናል በራሱ ስም ይከሳል፣ ይከሰሳል፣

፳· በግለሰቦች እጅ ያሉ የጦር መሣሪያዎችን ክልሉ በሚያ ወጣው ሕግ፣ ደንብና መመሪያ መሠረት ለይቶ ይመዘግባል አግባብ ላላቸው ፈቃድ ይሰጣል፣

፰· የኮሚሽኑ አቋም፣

ኮሚሽኑ፣

፩· በክልሉ መንግሥት የሚሾሙ አንድ ኮሚሽነርና፣ ምክትል ኮሚሽነር፣

፪· ኮሚሽነሩን፣ ምክትል ኮሚሽነሩንና ረዳት ኮሚሽነሮችን ያቀፈ የሥራ አመራር ጉባኤ እንዲሁም የክልል ኮሚሽነሮችና የዞን ፖሊስ ዴስክ ኃላፊዎች የጋራ ጉባኤ፣

፫· ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ የኃላፊነት ቦታዎችን የሚመሩ ኃላፊዎች፣ ፖሊሶችና ሌሎች የሲቪል ሰራተኞች

፬· በመተዳደሪያ ደንቡ የሚቋቋሙ ልዩ ልዩ ኮሚቴዎችና ንዑሳን ኮሚቴዎች ይኖሩታል።

፱· የኮሚሽኑ የስራ አመራር ጉባኤ ስልጣንና ተግባር፣

የስራ አመራር ጉባኤ፣

፩· ወንጀል ለመከላከልና ለመመርመር የሚረዱ በክልል ደረጃ የወጡ የፖሊሲ የስትራቴጂና የስታንዳርዳይዜሽን ጥናቶችን በመመርመር ከአስተያየት ጋር ለክልሉ ኮሚሽነሮችና ለዞን ፖሊስ ዴስክ ሀላፊዎች ጉባኤ እንዲቀርብ ያደርጋል፣

9) of the work relation hold between the Region's police commission and Federal Police Commission, issue a certificate of no criminal record;

10) conduct studies about the commission's consolidation, structure, performance and capacity building; and also to enhance crime prevention and investigation activities, and to enable that the efficiency and service of the police profession be similar and standardized in the whole country;

11) collect and analyse criminal data, traffic accidents and statistics at a Regional level, compile and report the data to the Regional State and the Federal Police;

12) exchange information and undertake co-ordinated committee activities with security organs and other Region's Police;

13) utilize capacity building training, professional and technical advice offered by the Federal Police;

14) accept, when it is deemed necessary, the delegation given to him by the Federal Police in accordance with Federal Police Commission establishment Proclamation No. 313/2002 Part Two Article 7 Sub-article 15;

15) delegate, as may be necessary, its powers to other organs and civil servants for the execution of certain functions;

16) consolidate the zonal and district police offices, monitor their operation, set up and administer the Region's police training school;

17) facilitate and participate the police officers in the internal and overseas training opportunities in order to upgrade the professional competence of the police;

18) establish relations and exchange information with the Federal and Regional Police Commissions;

19) enter into contracts, own property, sue and be sued in its own name;

20) register individually-handed weapons according to the rules, regulations and directives set by the region, and issue the license.

8. *Structure of the Commission*

The Commission shall have:

1) A commissioner and a Deputy Commissioner to be appointed by the Regional State;

2) A Management Council comprising the Commissioner, Deputy Commissioner and Assistant Commissioner, and also the joint Council of the Regional Commissioners and the Zonal Police Desk Heads;

3) Other Police Officers, Heads and Civil Servants necessary for its activities.

9. *Powers and Functions of the Management Council*

The Management Council shall:

1) examine studies on Regional Level, strategy and standardization required for the prevention and investigation of crimes, and submit the same to the Region's Commissioners and the Council of the Zonal Police Desk Heads, with its recommendation

፪· የኮሚሽኑን አደረጃጀት፣ አወቃቀር፣ አሰራርና አቅም ግንባታ የሚመለከቱ ጥናቶችን ይመረምራል፣ ሊወሰዱ የሚገባቸውን እርምጃዎች ከአስተያየት ጋር ለማስተባበሪያ ቢሮ ሀላፊው ያቀርባል፣

፫· በፌዴራሉ ፖሊስ የሚሰጡ የአቅም ግንባታና በከፍተኛ ስልጠናዎች ለመሳተፍ ዝግጅትና የተሳታፊዎች ምዘና ያደርጋል፣

፬· ለክልሉ ፖሊስ የተዘጋጀውን አመታዊ የበጀት ረቂቅ በመመርመር እንዲፀድቅለት በማስተባበሪያ ቢሮ ሀላፊ በኩል ለክልሉ መንግስት ያቀርባል፣

፭· የኮሚሽኑን አመታዊ ዕቅድ ፣ ሪፖርትና የስራ አፈፃፀምን በመገምገም የውሳኔ ሪፖርት ለማስተባበሪያ ቢሮ ያቀርባል፣

፮· ኮሚሽኑ ከሌሎች ክልል ፖሊስ ኮሚሽኖች ጋር መልካም የስራ ግንኙነት እንዲኖር ያደርጋል፣ የአዋሳኝ ክልል የፀጥታ ችግሮች ከተፈጠሩ በጋራ ያስወግዳል፣

፲· <u>የማስተባበሪያ ቢሮ ሀላፊ ስልጣንና ተግባር፣</u>

የማስተባበሪያ ቢሮ ሀላፊው

፩· የኮሚሽኑን አጠቃላይ የስራ እንቅስቃሴ ይከታተላል፣

፪· የኮሚሽኑን ረዳት ኮሚሽነሮችና የዞን ፖሊስ ሀላፊዎች ሹመትና ምደባ ያፀድቃል፣

፫· የኮሚሽኑን ዓመታዊ የሥራ አፈፃፀም ሪፖርት ፣ የሥራ ዕቅድ እና የበጀት ረቂቅ በመመርመር እንዲፀድቅ ያደርጋል፣

፬· በኮሚሽኑ ተዘጋጅቶ የሚቀርብለትን የአደረጃጀት፣ የአሰራርና የሰው ሀይል የአቅም ግንባታ መርሀ ግብርና ጥናቶችን ይመረምራል፣ ያፀድቃል፣

፭· አዋጁን ለማስፈፀም የሚረዱ ደንቦችና መመሪያዎች እንዲፀድቁ ያደርጋል፣

፲፩· <u>የኮሚሽነሩ ስልጣንና ተግባር፣</u>

፩· ኮሚሽነሩ ተጠሪነቱ ለማስተባበሪያ ቢሮ ኃላፊ ሆኖ የኮሚሽኑን ሥራና የዞን ፖሊስን በበላይነት ይመራል፣ ያስተባብራል፣

፪· የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ "፩" ጠቅላላ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ኮሚሽነሩ ፣

ሀ) የኮሚሽኑን ረዳት ኮሚሽነሮችና የዞን ፖሊስ ሀላፊዎች እንዲሾሙና እንዲመደቡ ለማስተባበሪያ ቢሮ ያቀርባል፣

ለ) የክልሉን ፖሊስ መተዳደሪያ ደንብ ያስፈጽማል፣

ሐ) በክልሉ በፖሊስነት ከተቀጠሩት ውጭ ያሉትን የድጋፍ ሰጭ ሲቪል ሠራተኞች በመንግሥት ሠራተኞች ሕግ መሠረት ያስተዳድራል፣

መ) በክልሉ ፖሊስ አቤቱታ ሰሚና የዲሲፕሊን ኮሚቴ እንዲሁም በዞን ፖሊስ የሚሰጡ ውሳኔዎችን በይግባኝ ሲቀርብለት ይወስናል፣

ሠ) የኮሚሽኑን ዓመታዊ የሥራ ዕቅድና ረቂቅ በጀት ለማስተባበሪያ ቢሮ ሀላፊው ያቀርባል በመንግሥት ሲፈቀድም በሥራ ላይ እንዲውል የበጀት ድልድሉን በጋራ ጉባኤ ያስወስናል፣

ረ) ለኮሚሽኑ በተፈቀደው በጀት መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፣

ሰ) የኮሚሽኑን አደረጃጀት፣ አወቃቀር አሰራርና አቅም ግንባታ የሚመለከቱ ጥናቶች ፣ የወንጀል መከላከልና ምርመራ ስራዎችን ለማሻሻል የሚረዱ ጥናቶች እንዲሁም የፖሊስ አገልግሎት ተመሳሳይነት ያለው ደረጃውን የጠበቀ እንዲሆን ለማድረግ የሚያስችሉ ጥናቶች እንዲከናወኑ ያደርጋል፣

ሸ) ከፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ጋር ግንኙነት ሳያቋርጥ የ24 ሰአትና ሳምንታዊ ተከታታይነት ያለው የመረጃ ልውውጥ ያደርጋል፣



2) examine studies pertaining to the organization, structure and operation of the Commission and submit measures to be taken with its recommendations to the Head of the Co-ordinating Bureau;

3) prepare and evaluate participants for the capacity building and higher training offered by the Federal Police;

4) look through the annual budget draft prepared for the Region's Police and submit the same to the Regional State through the Head of the Co-ordinating Bureau for approval;

5) evaluate the annual plan, report and performance of the commission and submit the final report to the co-ordinating Bureau.

6) maintain good working relations between the Commission and other Region's Police Commissions; mutually avoid security problems caused in the bordering regions.

10. *Powers and Functions of the Head of the Co-ordinating Bureau*

Head of the Co-ordinating Bureau shall:

1) follow up the overall activities of the Commission;
2) approve the appointment of the Assistant Commissioners of the Commission; and the Head of the Zonal Police;
3) look through and seek the approval of the annual plan, report, draft budget and performance of the Commission;
4) examine and approve the studies on the organization, performance, human resource and capacity building program submitted to him by the Commission;
5) take regulations and directives necessary for the implementation of this proclamation.

11. *Powers and Functions of the Commissioner*

1) The Commissioner shall be accountable to the Head of the Co-ordinating Bureau and direct and co-ordinate the overall activities of the Commission and the Zone's Police;

2/ Without prejudice to the generality of Sub-Article (1) of this Article, the Commissioner shall:

(a) recommend Assistant Commissioners of the Commission and Heads of the Zonal Police to be appointed and assigned by the Co-ordinating Bureau;
(b) execute Regulation of the Region's Police;
(c) administer the supporting staff, other than those employed;
(d) render a final decision on appeals lodged against the decisions of the Regional Police Complaint Hearing Organ and that of the Discipline Committee;
(e) submit the annual work plan and budget of the Commission to the Head of the Co-ordinating bureau and upon approval by the Government, for the implementation, approve the budget allocation by the joint Council;
(f) effect expenditures in accordance with the budget approved for the Commission;
(g) cause studies to be made with regard to the organization, structure, operation and building the capacity of the Commission, on the improvement of crime prevention and investigation activities; as well as on police service standardization;

ቀ) ኮሚሽነሩ ከፌደራል ፖሊስ ኮሚሽንና ከሌሎች ክልል ፖሊስ ኮሚሽኖች ጋር መልካም የስራ ግንኙነት እንዲኖር ያደርጋል፣

በ) የዞን ፖሊስ የስራ እንቅስቃሴዎችን በጥናት ፣ በመገምገም የወንጀል መከላከልና ምርመራ ስራዎችን የአቅም ግንባታ ተግባሮችን የችግራቸውን ደረጃ መሰረት በማድረግ እንደየቅደም ተከተላቸው እንዲያገኙ ያደርጋል፣

ተ) የኮሚሽኑን የአመራር ጉባኤና የዞን ፖሊስ ሀላፊዎች የጋራ ጉባኤ በሰብሳቢነት ይመራል፣

ቸ) የአጎራባች ክልል ፖሊስ የጋራ ፀጥታ ኮሚቴ ግንኙነት ሳይቋረጥ እንዲኖር በማድረግ ሂደቱን ይከታተላል፣

፲፪· የምክትል ኮሚሽነሩ ስልጣንና ተግባር፣

፩· ምክትል ኮምሽነሩ፣

ሀ) የኮሚሽኑን ተግባሮች በማቀድ በማደራጀት በመምራትና በማስተባበር ኮሚሽነሩን ይረዳል፣

ለ) በኮሚሽኑ መዋቅር መሰረት የስራ ክፍፍሎች በማድረግ ከኮሚሽኑ ዘርፎች ከፊሉን ይከታተላል፣

ሐ) ኮሚሽነሩ በማይኖርበት ጊዜ እርሱን ተክቶ ይሰራል፣

መ) በኮሚሽነሩ ተለይተው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል፣

፪· ምክትል ኮሚሽነሩ ተጠሪነቱ ለኮሚሽነሩ ይሆናል፣

፲፫· በጀት፣

የኮሚሽኑ በጀት በክልሉ መንግስት ይመደባል፣

፲፬· ስለ ሂሳብ መዛግብት፣

፩ ኮሚሽኑ የተሟላና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል፣

፪ የኮሚሽኑ የሂሣብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች የክልሉ ኦዲት ቢሮ በሚሰይመው ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራሉ።

ክፍል ሶስት

ስለ አፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት

ፖሊስ ኮሚሽን አስተዳደር

፲፭· ለፖሊስነት የሚያበቁ መመዘኛዎች፣

፩ በክልሉ ፖሊስነት ለመመልመል ፈቃደኛ የሆነ ኢትዮጵያዊ የሚከተሉትን መመዘኛዎች የሚያሟላ መሆን ይኖርበታል፣

ሀ) ለኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና ለክልሉ ሕገ መንግሥት ታማኝና ተገዢ የሆነ፣

ለ) የክልሉን የስራ ቋንቋ የሚችል፣

ሐ) በፖሊስነት ለመመልመል የሚያስፈልገው የትምህርት ደረጃ በመተዳደሪያ ደንቡ ላይ በሚወሰነው መሰረት ይሆናል፣

መ) አካላዊ ብቃትና የተሟላ ጤንነት ያለው፣

ሠ) መልካም ስነ ምግባር ያለው

ረ) በወንጀል የጥፋተኛነት ሪከርድ የሌለው፣

ሰ) ዕድሜው ከ18 ዓመት ያላነሰ፣

ሸ) የፖሊስ ምልመላ በሕዝብ ተሣትፎ ላይ የተመሰረተ ይሆናል።

፪· በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንድ መሰረት የተመለመለ ማንኛውም ሰው የፖለቲካ ድርጅት አባል የሆነ እንደሆነ በፖሊስነት ሲቀጠር የፖለቲካ ድርጅት አባልነቱን መተው ይኖርበታል።



(h) exchange information continously for 24 hours and weekly in series by establishing with Federal Police Commission;

(i) maintain good relations between the Commissioner and Federal Police Commission and other Regional Police Commissions;

(j) Preside over the Commission's Management Council and the Zonal Police Heads Joint Council;

(k) Follow up the continuity of the relationship of the neighbouring Region's Police mutual security committee.

12. *Powers and Functions of the Deputy Commissioner*

1) *The Deputy Commissioner shall:*

(a) assist the Commissioner in planning, organizing, directing and co-ordinating the functions;

(b) follow up part of the Commission's departments by sharing functions in accordance with the structure of the commission;

(c) act on behalf of the Commissioner in the absence of the latter;

(d) discharge other duties which may be specifically entrusted to him by the Commissioner.

2) The Deputy Commissioner shall be accountable to the Commissioner.

13. *Budget*

The Regional State shall allocate the budget of the Commission.

14. *Books of Accounts*

1) The Commission shall keep complete and accurate books of accounts.

2) The books of accounts and documents relating to finance shall be annually audited by the Auditor General designated by the Region's Audit Bureau.

*PART THREE*

*Administration of the Afar National Regional State Police Commission*

15. *Criteria for Recruitment of a Police Officer*

1) Any Ethiopian citizen to be recruited as a member of the Region's police shall have to fulfil the following requirements:

(a) faithful to the constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Region's Constitution;

(b) know the official language of the Region;

(c) the educational standard required for recruitment is in accordance with the Regulation;

(d) physical fitness and good health;

(e) have a good conduct;

(f) have no record of criminal convictions;

(g) not to be under the age of 18 years;

(h) the recruitment shall be on the people's participation.

2) Where any person recruited, in accordance with Sub-Article (1) of this Article, is a member of a politica orgaination, he shall quit his membership upoı employment.

፲፮· ቃለ መሐላ ስለመፈፀም፣

በፖሊስነት የተቀጠረ ማንኛውም ምልምል ለፌደራሉ ህገ–መንግስትና ለአፋር ክልል ህገ–መንግስት ታማኝ በመሆን የተጣለበትን ሕዝባዊ አደራና ሙያዊ ሀላፊነት ለመወጣት ቃለ መሐላ ይፈጽማል ፤ የቃለ መሀላውም ይዘት በደንቡ ይወሰናል።

፲፯· ለሲቪል የመንግሥት ሠራተኞች የፖሊስ ሥልጣን ስለመስጠት፣

፩· ልዩ ሙያ ለሚጠይቁ ጉዳዮች በክልል የመንግስት ሰራተኞች አዋጅ ለሚተዳደሩ የመንግሥት ሠራተኞች የፖሊስ ሥልጣን ሊሰጥ ይችላል፤

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ መሠረት የሚሰጠው የፖሊስ ሥልጣን ለጉዳዩ አስፈላጊ በሆነው መጠን ብቻ ይሆናል።

፲፰· የአገልግሎት ዘመን፣

፩· የማንኛውም ፖሊስ የግዴታ አገልግሎት ዘመን ሰባት ዓመት ይሆናል። ዝርዝር አፈጻጸሙም በሚወጣው ደንብ ይወሰናል፤

፪· የማንኛውም ፖሊስ ቅጥር በሚከተሉት ምክንያቶች ይቋረጣል፤

ሀ) በሞት፤

ለ) በደንቡ መሠረት የስንብት ጥያቄ ቀርቦ ተቀባይነት ሲያገኝ፤

ሐ) በሐኪም ቦርድ በተረጋገጠ ሕመም ወይም በአካል ጉዳት ምክንያት ለሥራው ብቁ ሣይሆን ሲቀር፤

መ) በፍርድ ቤት በወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ ከተገኘና በደንቡ መሠረት ወንጀሉ ለሥራው ብቁ አያደርገውም ተብሎ ሲወሰን፤ ዝርዝሩ በሚወጣው ደንብ ይወሰናል።

ሠ) በሥራ አፈጻጸም ወይም በዲሲፕሊን ጥፋት፤

ረ) በጡረታ ሲገለል፤

፲፱· መብት፤

፩· ማንኛውም የክልሉ ፖሊስ አባል፤

ሀ) በመንግሥት በሚፀድቅ የደመወዝ እስኬል ያገኛል፤

ለ) በኮሚሽኑ የመተዳደሪያ ደንብ መሠረት ቀለብ ፤ ልዩ ልዩ አበሎች፣ የደንብ ልብስና የህክምና አገልግሎት ያገኛል፤

ሐ) በጡረታ ሕግ መሠረት የጡረታ መብት ይኖረዋል፤

መ) ሥራውን በተገቢው መንገድ በመወጣት ላይ እያለ ለሚደርስበት ተጠያቂነት በመሥሪያ ቤቱ ወጭ የጥብቅና አገልግሎት ያገኛል። ዝርዝር አፈጻጸሙ በሚወጣው ደንብ ይወሰናል፤

ሠ) በማንኛውም አጋጣሚ የበላይ ኃላፊዎችን በአግባቡ የመጠየቅ፣ ስህተት ሲያይ የመጠቆም ፤ በውይይት ችግሮችን የመፍታት፣ እንዲሁም የሥልጣን ተዋረድን ጠብቆ አቤቱታ ማቅረብ ይችላል፤

ረ) ከሥራው ጋር በተያያዘ ሁኔታ በሚደርስበት ጉዳት ዘላቂ ሙሉ ወይም ከፊል የመስራት ችሎታውን ያጣ ፖሊስ አግባብ ባለው የጡረታ ህግ የተሰጠው መብት ይከበርለታል፤

፳· ግዴታ፤

ማንኛውም የክልሉ ፖሊስ አባል

፩· በሕገ መንግሥቱ የተረጋገጡትን የዜጎች ሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች ሣይሸራረፉ በማክበር በወንጀለኛ መቅጫ ህግ፣ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርአት ሕግና በሌሎች ሕጐች መሠረት ሥራውን የማከናወን፤

16. *Oath*

Any police recruit shall take oath upon employment declaring that he carries out his functions with diligence and utmost commitment to the Federal and Afar Region's Constitution so that he fulfills the demands of public trust and professional responsibility bestowed on him. Contents of the oath shall be determined by the Regulation.

17. *Delegation of Police Powers to Civil Servants*

1) Police powers may be delegated to a civil servant, administered under the Region's Civil Service Proclamation, for cases that require special skill.
2) The police power to be delegated pursuant to Sub-Article (1) of this Article shall be only to the extent that may be required for the matter.

18. *Terms of Service*

1) Any police officer shall be employed for a seven years obligatory service; particulars for its implementation shall be determined by the Regulation.
2) The service of any police officer shall be terminated for any of the following reasons:
   (a) upon death;
   (b) where a request for a release is accepted in accordance with the relevant Regulation;
   (c) when a medical board testifies the unfitness of the police officer for the job on account of illness or bodily injury;
   (d) when the police officer is found guilty by a court of law and it is decided in accordance with the regulation that the conviction shall not make him fit for the job. Particulars shall be determined the by Regulaltion;
   (e) owing to inefficiency report or disciplinary misconduct;
   (f) upon retirement;

19. *Rights*

1) Any Regional Police officer shall:
   (a) get a salary in accordance with the salary scale approved by the Government;
   (b) be entitled to rations, various allowances, uniforms and medical services in accordance with the administrative regulations of the Commission;
   (c) be entitled to a pension in accordance with Pension Laws;
   (d) be provided with attorney services by the expense of the Commission for liabilities he incurs while properly discharging his responsibilities. Particulars shall be determined by the Regulations;
   (e) have the right to appropriately question superiors under any circumstances; inform mistakes; resolve problems through discussion as well as lodge complaints following the chains of command;
   (f) be entitled to benefits provided in the relevant pension law for permanent, total or partial disability sustained in relation to his duties;

20 *Duties*

Any Regional Police officer has the duty:

1) to perform his activities in accordance with the Criminal Procedural Code and other relevant laws by fully observing human and democratic rights ensured by the Constitution;

፪· ፖሊሳዊ ሥራውን ሲያከናውን ማንነቱን የሚገልፅ መታወቂያ የማሣየት ግዴታ አለበት፤

፳፩· <u>የጡረታ መውጫ ዕድሜ፤</u>

ማንኛውም የክልሉ ፖሊስ አባል በጡረታ የሚገለልበት ዕድሜ ጣሪያ ለመንግስት ሰራተኞች የተወሰነው የጡረታ መውጫ ዕድሜ ይሆናል፤

፳፪· <u>የክልሉ ፖሊስ አቤቱታ ሰሚ፤</u>

በኮሚሽኑ ውስጥ የህዝብ አቤቱታ የሚሰማ የክልሉ ፖሊስ አቤቱታ ሰሚ አካል ይቋቋማል፤ ዝርዝሩ ኮሚሽኑ መተዳደሪያ ደንቡን ተከትሎ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።

## ክፍል አራት

### ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

፳፫· <u>የክልሉ ፖሊስ ኮሚሽን ከፌዴራል ፖሊስና ከሌሎች ክልል ፖሊስ ኮሚሽኖች ጋር ስለሚኖረው የስራ ግንኙነት፤</u>

፩· ኮሚሽኑ ከፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ጋር ወንጀልን ለመከላከልና ለመመርመር በቅንጅትና በተደጋጋፊነት ይሰራል፤

፪· ከፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን በሚሰጠው ውክልና መሰረት በፌዴራል ፍርድ ቤት ስልጣን ስር የሚወድቁ የወንጀል ጉዳዮችን ሲመረምርና ሲከላከል ተጠሪነቱ ለፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን ይሆናል፤

፫· የክልሉ ፖሊስ ኮሚሽን የፌደራሉ ፖሊስ ኮሚሽንና የሌሎች ክልል ፖሊስ ኮሚሽኖች በሚያደርጉት የጋራ ጉባኤ ተሣታፊ ይሆናል፤

፳፬· <u>የክልሉ ፖሊስ ኮሚሽነሮች እና የዞን ፖሊስ ዴስክ ሀላፊዎች ጉባኤ</u>

፩· የኮሚሽኑና የዞን ፖሊስ ሀላፊዎች በአመት ቢያንስ ሁለት ጊዜ የጋራ ጉባኤ ያደርጋሉ፤ የጋራ ጉባኤውን ውሳኔና ተሳትፎ የሚሹ አስቸኳይ ጉዳዮች ካሉ በጥሪ ይሰባሰባሉ የጋራ ጉባኤውን የክልሉ ፖሊስ ኮሚሽነር ይመራል፤ የጋራ ጉባኤውም፡–

ሀ) የክልሉን ፖሊስ ዕቅድ ለመተግበር የአሰራር ስልቶችን ይቀይሳል፤

ለ) የፀጥታ ችግሮች፣ የወንጀል መከላከልና ምርመራ፣ የትራፊክ ስራዎችን በመገምገም በሚቀርቡ ጥናቶች ላይ በመነጋገር የተሻለ አሰራር እና ውጤት እንዲኖር ያደርጋል፤

ሐ) የክልሉን ፖሊስ የስልጠና ዕቅዶች አቅጣጫ ይነድፋል፤

፪· ኮሚሽኑ የጋራ ጉባኤው ያስተላለፋቸውን ውሳኔዎች መተግበራቸውን ይገመግማል ይከታተላል፤

፫· ለክልሉ መንግስት ቀርቦ የፀደቀውን በጀት በጋራ ይደለድላሉ፤

፳፭· <u>ወታደራዊ ማዕረግ ስለመቅረቱ፤</u>

፩· በማናቸውም ደረጃ የሚገኝ የክልል ፖሊስ አባል ወታደራዊ ማዕረግ አይኖረውም፤ ሆኖም የፖሊስ የሆነ ማዕረግና ምልክት ይኖረዋል ዝርዝሩ በሚወጣው ደንቡ ይወሰናል።

፪· ማንኛውም የክልሉ ፖሊስ የሥራ መደቡን የሚያመለክት የመለያ ደንብ ልብስ እንዲሁም ማንነቱን የሚገልፅ ሥሙን ፣ መለያ ቁጥሩን፣ ኃላፊነቱን የያዘ ባጅ ወይም ምልክት ይኖረዋል፤

፳፮· <u>አሠራር፤</u>

፩· በክልሉ ፖሊስ ኮሚሽን መዋቅር በየደረጃው ባሉት ኃላፊዎችና ሠራተኞች የቡድን አሠራር ዋና የተግባር አፈጻጸም አቅጣጫ ይሆናል። የቡድን አሰራሮች የጋራና የነጠላ ሀላፊነትን ያስከትላሉ።

2/ to show his identity card while carrying out his police duties;

21. *Retirement*

The retirement age limits for any member of the Regional Police shall be the age determined by the Pension Laws for Civil Servants.

22. *Complaints Hearing Organ*

There shall be established a Regional Police Complaint Hearing Organ that hears complaints of the Public. Particulars shall be determined by directives to be issued by the Commission.

## *PART FOUR*

### *Miscellaneous Provisions*

23. *Relations of the Regional Police Commission with the Federal Police and other Region's Police Commissions*

1/ The Commission shall work in cooperation and mutually supportive way with the Federal Police Commission in the prevention and investigation of crimes.

2/ The Federal Police Commission shall be accountable to the Commission when they prevent and investigate criminal cases falling under the jurisdiction of the Federal Courts in accordance with the delegation given to them.

3/ The Region's Police Commission shall preside over joint meetings held by the other Region's Police Commissions and the Federal Police Commission.

24. *Council of the Region's Police Commissioners and Head of the Zonal Police Desk*

1/ The Commission and Heads of the Zone's Police shall hold joint council at least twice in a year. For urgent issues deserving the joint councils decision, there shall be called a meeting. The joint council shall be chaired by the Region's Police Commissioner.

The Joint Council shall:

(a) devise means to implement the Region's Police plan.

(b) make a better operation and seek output through discussing and analyzing the submitted studies on security conditions, crime prevention and investigation and traffic offences;

(c) devise direction with respect to the Region's Police training.

2/ The Commission shall follow up the implementation of the decisions adopted by the joint council.

3/ Jointly allocate the budget approved by the Regional State.

25. *Abandonment of Military Rank*

1/ No police officer, at any level, shall have a military rank; however; there shall be a police rank and badge as a substitute. Particulars shall be determined the by regulation.

2/ Any police officer shall have uniforms that indicate his position as well as a badge or sign showing his name, number, department and responsibility.

26. *Performance*

1/ Team performance by officials and employees at all levels of the structure of the Region's Police Commission shall be the main operational perspective. Team performance shall entail joint and several liabilities.

፪· በክልሉ ፖሊስ ኮሚሽን መዋቅር በየደረጃው የሚገኙ ኃላፊዎች በተሰጣቸው ሥልጣን መሰረት በመወሰን ኃላፊነታቸውን የመወጣት ግዴታ አለባቸው።

፫· የፖሊስ አሰራር የተጠያቂነትና የግልፅነት መርህ የተከተለ መሆን ይኖርበታል፤

፬· የፖሊስ አሠራር የሕዝብ ተሣትፎን መሠረት ያደረገ መሆን ይኖርበታል፤

፳፯· <u>የተከለከለ ድርጊት፤</u>

ማናቸውም ኢሰብአዊ ወይም ክብርን የሚነካ አያያዝና ድርጊት የተከለከለ ነው።

፳፰· <u>የሕጉ ተፈጻሚነት፤</u>

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ሕግ ተፈጻሚነት አይኖረውም፤

፳፱· <u>ደንብ የማውጣት ሥልጣን፤</u>

የክልሉ መንግሥት መስተዳድር ምክር ቤት ካቢኔ ይህን አዋጅ ተከትሎ ደንብ የማውጣት ሥልጣን ይኖረዋል።

፴· <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ፤</u>

ይህ አዋጅ በአፋር ክልል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት
ምክር ቤት

——ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ/ም
ሠመራ
እስማኤል አሊ ሴሮ

የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ርዕስ መስተዳደር



2/ The officials at all levels of the structure of the Region's Police Commission shall discharge their responsibilities in accordance with their allocated functions.

3/ The operation of the Commission shall be based on the principles of accountability and transparency

4/ Activities of the Commission shall be based on participation of the public.

27 *Prohibited Activities*

Any inhuman or degrading treatment or act is prohibited.

28 *Applicability of Laws*

Any law inconsistent with this Proclamation shall not be applicable.

29 *Power to Issue Regulations*

The Regional State Administrative Council cabinet shall issue Regulations pursuant to this Proclamation.

30 *Effective Date*

This Proclamation shall come into force on the date of its publication on the Afar Region's Negarit Gazeta.

The Afar National Regional
State Council
Done at Semera, this...... day of May 2003
Ismael Ali Saero
Chief Administrator of the Afar
National Regional State Council

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት

የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት

# የአፋር ክልል ነጋሪት ጋዜጣ
# AFAR REGION NEGARIT GAZETA

OF THE AFAR NATIONAL REGIONAL STATE

ሁለተኛ ዓመት ቁጥር ፬
ሠመራ የካቲት ፳፯ ቀን ፲፱፻፺፮ ዓ/ም

በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት
ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

2nd Year No. 4
SEMERA – 6th March 2004

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፳፫/፲፱፻፺፮ ዓ.ም
የአፋር ብሔራዊ ክልል መንግሥት የኢንቨስትመንት
አዋጅ ............................................................ ገጽ ፩

CONTENTS

Proclamation No. 23/2004
The Afar Regional State Investment
Proclamation ............................................... Page 1

## የአፋር ብሄራዊ ክልል መንግሥት ኢንቨስትመንት ጽ/ቤት
## የተሻሻለው የኢንቨስትመንት አዋጅ

የአፋርን የኢኮኖሚ ልማት ለማፋጠንና የኑሮ ደረጃውን ለማሻሻል ኢንቨስትመንትን ማበረታታትና ማስፋፋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የክልሉን ኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ ለማጠናከር የሀገር ውስጥና የውጭ ባለሃብቶች ተሳትፎ ማስፋፋትና ሁኔታዎችን ማመቻቸት በማስፈለጉ፤

እነዚህን ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ በሥራ ላይ ያለውን የኢንቨስት መንት ህግ በተሻሻለ ህግ መተካቱ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ—መንግሥት አንቀጽ ፶፪ ንዑስ አንቀጽ ፪/ለ/ በአፋር ብሔራዊ ክልል መንግሥት ህገ—መንግሥት አንቀጽ ፵፯ ንዑስ አንቀጽ ፪/ለ/ለክልል መንግሥት በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

### ክፍል አንድ
### ጠቅላላ

አንቀጽ ፩ አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ የአፋር ብሄራዊ ክልል መንግሥት የኢንቨስ ትመንት አዋጅ ቁጥር ፳፫/፲፱፻፺፮ ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## PROCALAMTION NO.
## INVESTMENT PROCLAMATION OF THE STATE OF AFAR THE STATE OF AFAR INVESTMENT PROCLAMATION

WHEREAS, it has been found necessary to promote and expand investment with a view to speeding up the economic development of the region and improve the living standards of its people;

WHEREAS, it has become essential to create a conducive environment and thereby increase the participation of domestic as well as foreign investors with a view to strengthening investment activities in the region;

WHEREAS, it has beomce necessary to tramline the system of administration of investment activities in the region;

NOW, THEREFORE, to attain these objectives; in accordance with Art. 52 (2) of the Consititution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and Art. 47 (2) (b) of the Constitution of the State of Afar; it has hereby proclaimed as followes:

### SECTION ONE
### *General*

1. *Short Title*

This Proclamation may be cited as the ''The Afar Regional State Investment Proclamation No. 23/2004''

አንቀጽ ፪ የተሻሻለው የ፲፱፻፺፯ ዓ.ም የኢንቨስትመንት አዋጅ ስለመጽደቁ

የጸደቀው የክልሉ ኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር ፭/ ፲፱፻፺፩ ዓ.ም ድንጋጌዎች ተሽረው የተሻሻለው የአፋር ክልል ኢንቨስትመንት አዋጅ በዚህ አዋጅ ጸድቋል።

አንቀጽ ፫ ትርጉም

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፤

፩· "ኢንቨስትመንት" ማለት አዲስ ድርጅት ለማቋቋም ወይም ነባር ድርጅትን ለማስፋፋት ወይም ለማሻሻል በባለሀብት የሚደረግ የካፒታል ወጪ ነው።

፪· "ማስፋፋት ወይም ማሻሻል" ማለት የነባር ድርጅትን የሙሉ አቅም ምርት ወይም አገልግሎት ከ፳፭% በላይ በእሴት ማሳደግ ሲሆን ይህም በዓይነት ወይም በመጠን ወይም በሁለቱም መጨመርን የሚያጠቃልል ነው።

፫· "ድርጅት" ማለት ለትርፍ ሲባል የተቋቋመ ድርጅት ነው።

፬· ካፒታል ማለት የሚተላለፍ ሰነድ የማምረቻ ወይም የአገልግሎት መስጫ መሣሪያ ህንጻ ማደሻ የሥራ ማስኬጃ መብት የፓቴንት መብት ወይም ሌላ የንግድ ሃብት ነው።

፭· "ሰው" ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው ድርጅት ነው።

፮· ባለሃብት ማለት በክልሉ ኢንቨስትመንት ያደረገ ባለሀብት ነው ወይም እንደቃሉ አገባብ ለአገር ውስጥ ባለሃብት እና ለውጭ ባለሃብት በኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር ፪፻፹/፲፱፻፺፬ አንቀጽ ፪ ንኡስ አንቀጽ/፭፣፮/እና በአዋጅ ቁጥር ፫፻፸፭/፲፱፻፺፮ /እንደተሻሻለ/የተሰጠውን ትርጉም ይሰጣል።

፯· ክልል ማለት የአፋር ብሔራዊ ክልል መንግሥት ነው።

፰· ጽህፈት ቤት ማለት የኢንቨስትመንት ጽህፈት ቤት ማለት ነው።

፱· የኢንቨስትመንት ኮሚቴ ወይም አካል ማለት በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የኢንቨስትመንት ቦርድ፣ የኢንቨስትመንት ጽ/ቤት ወይም የዞንና የወረዳ ኢንቨስትመንት ኮሚቴ ነው።

፲· ቦርድ ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፯ የተመለከተው አካል ነው።

፲፩· "የሚመለከተው አካል ወይም አግባብ ያለው የኢንቨስትመንት መ/ቤት" ማለት የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ወይም የአፋር ኢንቨስትመንት ጽ/ቤት ማለት ነው ።

አንቀጽ ፬ የተፈፃሚነት ወሰን

የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች በማዕድንና ነዳጅ ፍለጋ ምርመራና ማምረት ሥራዎች በሚደረግ ኢንቨስትመንት ላይ ተፈጻሚ አይሆንም።

ክፍል ሁለት
ስለ ኢንቨስትመንት ዓላማዎች

አንቀጽ ፭ ስለኢንቨስትመንት ዓላማዎች

በዚህ አዋጅ መሰረት አግባብ ያለው የኢንቨስትመንት መ/ቤት ወይም የኢንቨስትመንት አካላት የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል።

ሀ) የክልሉን ማህበራዊ አገልግሎት ማጐልበትና የኢኮኖሚ እድገቱን ማበረታታት

ለ) የክልሉን ህብረተሰብ በምግብ ራሱን እንዲችል ከሚመለከታቸው አካላት ጋር አስፈላጊ ሁኔታዎች ማመቻቸትና ማጠናከር።

2. The Afar Regional State Proclamation No. 5/1998 is repealed and hereby replaced by this revised Investment Proclamation of the Afar National Regional State.

3. *Definitions*

In this Proclamation, unless the context otherwise requires:

1) "Investment" means expenditure of capital by an investor to establish a new enterprise or to expand or upgrade one that already exists;
2) "Expansion/Upgrading" means increasing in value, by more than 25%, of the full production or service capacity of an existing enterprise, be it in variety, volume, or both.
3) "Enterprise" means an understanding established for purpose of gaining profit;
4) "Capital" means local or foreign currency, negotiable instruments, machinery or equipment, building, initial working capital, property rights, patent rights or other business assets,
5) "Person" means a natural or juridical person;
6) "Investor" means an investor having invested in the Region or shall have the meaning given to domestic investor and foreign investor under Art. 2(5) (6) of Investment Proclamation No. 280/2002 and Proc. 375/2004 (as amended);
7) "Region" means the Afar National Regional State;
8) "Office" means the Office of Investment;
9) "Investment Committee" means the Investment board of the Afar State Council and may refer, as the case may be, Zonal and District (Woreda) Investment Committees.
10) "Board" means the organ specified in Art. 7 of this Proclamation;
11) "The appropirate investment organ" means the Ethiopian Investment Commission or the Afar Investment Office.

4. *Scope of Application*

The provisions of this Proclamation shall not be applied to investment in prospecting, exploration a and development of minerals and petroleum resources.

SECTION TWO
*Investment Objectives*

5. *Investment Objectives*

Under this Procalmation, the appropirate investment office or ogan shall have the following objectives:

(a) to promote social services and accelerate the economic development of the Region;
(b) to create conducive environments; in collaboration with the appropriate authority; and strenghten its ties with same in order to make the population of the Region self-sufficient in food;

ሐ) የክልሉን ኅብረተሰብ በተለይም ግብርና ኢንዱስትሪ እንዲሁም የዘመናዊ ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ እንዲሆን ማበረታታት

መ) የክልሉን ሰፊ የተፈጥሮ ኃብት ጥቅም ላይ ለማዋልና ለማልማት ኢንቨስተሮችን ማበረታታት

ሠ) የክልሉን የገቢ ምንጭ ማሳደግ

ረ) ወደ ውጭ የሚላኩ የክልሉ ምርቶች በመጠን በጥራትና በዓይነት እንዲያድግ ማበረታታት

ሰ) የክልሉን ኅብረተሰብ ሰፊ የሥራ እድል መክፈት

ሸ) የውጭ ኢንቨስትመንት በክልሉ የኢኮኖሚ ልማት ተገቢውን ሚና እንዲኖረው ማድረግ

ክፍል ሦስት
የኢንቨስትመንት አስተዳደር አካላት

አንቀጽ ፮ የኢንቨስትመንት አካላት

፩· በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የኢንቨስትመንት አስተዳደር አካላትእንደገና በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።

፪· የኢንቨስትመንት አካላት የሚከተሉትን ክፍሎች ያካትታል።

ሀ) ቦርድ

ለ) የክልል ኢንቨስትመንት ጽ/ቤት

ሐ) የዞን ኢንቨስትመንት ኮሚቴ

መ) የወረዳ ኢንቨስትመንት ኮሚቴ

ንኡስ ክፍል አንድ
ስለ ኢንቨስትመንት ቦርድ

አንቀጽ ፯ ስለኢንቨስትመንት ቦርድ መቋቋም

፩· በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የኢንቨስትመንት ቦርድ የራሱ ጽ/ቤት ሲኖረው የጽ/ቤቱ ሥልጣንና ተግባርም በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፱ መሠረት ከቦርድ ሥልጣንና ተግባር ጋር በተመሳሳይ ተፈጻሚ ይሆናል።

፪· የኢንቨስትመንት ቦርድ የንግድ ኢንዱስትሪ ትራንስፖርት ሥራና ከተማ ልማት ማስተባበሪያ ቢሮ ኃላፊ የሚወሰን ቁጥር ያላቸው አባላት ይኖሩታል።

፫· የቦርዱ አባላት ከመንግሥትና ከግሉ ሴክተር የተውጣጡ ይሆናሉ።

፬· ቦርዱ ከዚህ ቀጥሎ የተዘረዘሩት አባላቶች ሲኖሩት በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ /፪/ መሰረት የን/ኢ/ት/ከ/ል/ማስተባበሪያ ቢሮ ኃላፊ እንደአስፈላጊነቱ የአባላቶቹን ብዛት ለመቀነስም ሆነ ለመጨመር ይችላል።

ሀ) ቦርዱ ተጠሪነቱ ለክልሉ ንግ/ኢን/ት/ስ/ከ/ል/ማስ/ሲሆን ቢሮ ኃላፊው የቦርዱ ሰብሳቢ ይሆናል።

ለ) ኢንቨስትመንት ጽ/ቤት ኃላፊ ········ ጸሀፊና አባል ይሆናል።

ሐ) የፋይናንስ ኢኮኖሚ ልማት ማስተባበሪያ ቢሮ ኃላፊ ·················· አባል

መ) የአርብቶ አደር ገጠር ልማት ማስተባበሪያ ቢሮ ኃላፊ ········· አባል

ሠ) ንግድ ኢንዱ/ትራንስፖርት ቢሮ ኃላፊ ············· አባል

ረ) ሥራና ከተማ ልማት ቢሮ ኃላፊ ·············· አባል

ሰ) የውሃ ሀብት ማዕድንና ኢነርጂ ቢሮ ኃላፊ ················ አባል

ሸ) የእንስሳትና እርሻ ልማት ቢሮ ኃላፊ ············ አባል

ቀ) የመስኖ ልማትና መጠጥ ውሃ ኮንስትራክሽን ባለ ሥልጣን ······················ አባል

በ) ባ·ቱ·ማ· ቢሮ ኃላፊ ···················· አባል

(c) to encourage the population of the Region to be beneificaries to modern-technology especially in the fields of agro-industry;

(d) to encourage investors to invest so as to exploit and develop the immense natural resources of the Region;

(e) to increase the sources of income of the Region;

(f) to encourage the increase in volume, quality and variety of export items of the Region;

(g) to create employment opportunities of population of the Region;

(h) to render foreign investment to play its proper role in the region's economic development,

*SECTION THREE*
*Investment Administration*

6. *Investment Administration Organs*

1) In the Afar National Regional State, the investment administration organ is hereby reestablished;
2) The administration of investment shall be carried out through the following organs:
   (a) a Board;
   (b) a Regional Investment Office;
   (c) a Zonal Investment Committees; and
   (d) a Woreda Investment Committee

*SUB SECTION ONE*
*Investment Board*

7. *Establishment of Investment Board*

1) The Investment Board of the Afar National Regional State shall have its own secretariat. The powers and duties of the secretariat are similar to the powers and duties of the board stated under Art. 9 of this Proclamation,
2) The number of members of the Investment Board shall be determined by the head of industry, transport, Public Works and Urban Development Coordinating Bureau.
3) The members of the board shall be drawn from government and private sector.
4) The board shall have the following members; where necessary, head of industry, transport, Public Works and urbam Development Coordinating Bureau increase or decrease the number of members purusant to Sub-Art. (2) of this provision
   (a) The Board is accountable to the Regional Trade, Industry, Transport, Public Works and Urban Development Coordinating Bureau. The head of the office is the chairperson of the Board.
   (b) Head of the investment Office .... Member and Secretary
   (c) Head of Finance and Economic Development Coordinating Bureau ........................ Member
   (d) Head of the Pastoralist and Rural Developing Coordinating................ ''
   (e) Head of Trade, Industry and Transport Bureau........................................ ''
   (f) Head of the Public Works and Urban Development Bureau ........................ ''
   (g) Head of Water, Mines and Energy Bureau ........................................................ ''
   (h) Irrigation Development and Water Construction Authority ............................ ''
   (i) Head of Culture, Tourism and Information Bureau.......................................... ''

አንቀጽ ፰ ስለቦርዱ ስብሰባዎች

፩· ቦርዱ በወር አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በማናቸውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል።

፪· ከቦርዱ አባላት ከግማሽ በላይ የሚሆኑት በቦርድ ስብሰባ ላይ ከተገኙ ምልዐተ ጉባኤ ይሆናል።

፫· የቦርዱ ውሳኔዎች በድምጽ ብልጫ ያልፋሉ ሆኖም ድምጽ እኩል በእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል።

አንቀጽ ፱ የቦርድ ሥልጣንና ተግባር

፩· የዚህን አዋጅ አፈጻጸምና የኢንቨስትመንት ሥራዎች በበላይነት ይቆጣጠራል ይመራል።

፪· በኢንቨስትመንት ፖሊሲው ላይ ለሚነሱ ጉዳዮች ውሳኔ ይሰጣል።

፫· ይህንን አዋጅ መሰረት ያደረገ ደንብ ለማውጣትና ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎች ያወጣል።

፬· በኢንበስትመንት ፍቃድና ከማበረታቻዎች አሰጣጥ ጋር በተያያዘ በሚቀርበት የይግባኝ አቤቱታ ላይ ውሳኔ ይሰጣል።

፭· ጽ/ቤቱ ለሚሰጠው አገልግሎት የሚያስከፍለውን ክፍያ ይወስናል።

፮· የጽ/ቤቱን ድርጅታዊ መዋቅርና ሠራተኞች የሚተዳደሩበትን መመሪያ ያጸድቃል።

፯· በየጊዜው የሚያወጣውን መመሪያ ኢንቨስተሮች በግልጽ እንዲያውቁት ያደርጋል።

፰· የክልሉን ኢንቨስትመንት ለማበረታታት አስፈላጊ መመሪያዎች ያወጣል።

፱· የኢንቨስትመንት ማበረታቻ ደንብ እና ሌሎች የኢንቨስትመንት ሥራን ሊያበረታቱ የሚችሉ ደንቦችን እንደአስፈላጊነቱ እንዲሻሻልና እንዲወጣ ለክልሉ መንግሥት መስተዳድር ም/ቤት ቀርቦ እንዲጸድቅ ለክልሉ መንግሥት ም/ቤት የህግና አስተዳደር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ያቀርባል።

፲· የዞን የወረዳ ኢንቨስትመንት ኮሚቴ ያቋቁማል ያደራጃል ይቆጣጠራል ይከታተላል።

፲፩· የአዋጁን አፈጻጸምና ተጓዳኝ ጉዳዮችን ይወስናል ተግባራዊነታቸውንም ያረጋግጣል።

፲፪· ለተፈቀደ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክት የመሬት ጥያቄ የቀረበለት የክልል ቦርድ የፌዴራልና የክልሉን ኢንቨስትመንት አዋጅና የማበረታቻ ደንቡን መሰረት በማድረግ ጥያቄው በቀረበለት በ፴ ቀን ውስጥ የተጠየቀውን መሬት በኢንቨስትመንት ጽ/ቤት አካላት በኩል ለባለሀብቱ ያስረክባል።

፲፫· ይህንን አዋጅና ሌሎች ደንቦችን መሰረት በማድረግ በቦርድ የተላለፉ ውሳኔዎች ተፈጻሚ የሚሆኑት በኮሚቴው ሲጸድቅ ብቻ ይሆናል።

ንኡስ ክፍል ሁለት

ስለኢንቨስትመንት ጽ/ቤት

አንቀጽ ፲ የኢንቨስትመንት ጽ/ቤት

፩· የኢንቨስትመንት ጽ/ቤት ራሱን የቻለ የህግ ሰውነት ያለው መ/ቤት ሆኖ ተጠሪነቱ ለአፋር ብ/ክ/መንግሥት ንግድ ኢንዱስትሪ ትራንስፖርት ከተማ ልማት ማስተባበሪያ ሲሆን የጽ/ቤቱ ኃላፊ በክልሉ መንግሥት ርእሰ መስተዳድር አቅራቢነት ይሾማል።

፪· የጽ/ቤቱ ኃላፊና ባለሙያዎች፣ ድጋፍ ሰጭ ሰራተኞች ይኖሩታል።

8. *Meeting of the Board*

1) The Board shall hold a regular meeting once in a month. However, it may hold extraordinary meetings at any time when necessary.
2) There shall be a quorum where more than half of the members are present at meetings of the Board.
3) Decisions of the Board shall be passed by a majority vote; in case of a tie, however, the chairman shall have a casting vote.

9. *Powers and Duties of the Board*

The Board shall have the following powers and duties:

1) to supervise and direct, as the superior authority, the implementation of this Proclamation and investment activities;
2) to decide on investment policy issues;
3) to issue directives necessary for the implementation of this Proclamation and regulaltions issued hereunder;
4) to decide on appeals submitted to it by investors with respect to the issuance of investment permits and the granting of incentives;
5) to determine service fees to be charged by the office;
6) to approve the organizational structure and personnel regulations of the office;
7) to publicly notify investors of directives issued by it from time to time;
8) to issue directives in order to encourage investment in the Region;
9) whenever it seems necessary, initiate investment incentive regulations or an amendment thereto and submit same to the State Council (Regional State Council) for approval;
10) to establish and organize Zonal and Woreda investment committees and supervise and follow up their activites;
11) to decide on ways of implementation of matters provided for in this Proclamation and related matters and ensure their implementation;
12) where the regional government receives an application for the allocation of land for an approved investment, it shall, on the basis of the Federal and its own investment law and investment incentive Regulation, deliver within 30 days, the required land to the investor;
13) decisions passed on the basis of this Proclamation and other laws by the Board shall become effective only where approved by the committee.

10. *The Investment Office*

1) The Investment Office is an autonomous public institution having legal personality. The office shall be accountable to the Trade & Industry, Transport Urban Development Cooridinating Bureau of the Afar National Regional State. The head of the office shall be appointed upon recommendation of the president of the Regional State.
2) The Office shall have a head and the necessary staff;

አንቀጽ ፲፩· <u>የኢንቨስትመንት ጽ/ቤት ኃላፊ ሥልጣን ተግባር</u>

፩· የዚህን አዋጅ አፈጻጸምና ተጓዳኝ ጉዳዮች ተግባራ ዊነታቸውን ያረጋግጣል።

፪· በዚህ አዋጅ በአንቀጽ ፲፪ የተዘረዘሩት ሥራዎች በጽ/ቤቱ እንዲተገበሩ ሁኔታዎችን ያመቻቻል ተግባራዊ መሆናቸውንም ያረጋግጣል።

፫· የጽ/ቤቱን የሥራ ፕሮግራምና በጀት አዘጋጅቶ ለክልል መንግሥት መስተዳድር ም/ቤት ያቀርባል ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል።

፬· ለጽ/ቤቱ በተፈቀደው በጀት መሰረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል። በህጉ መሰረት ተፈላጊ የሆኑት ሰራተኞች እንዲቀጠሩ ያደርጋል።

፭· የጽ/ቤቱን የሥራ እንቅስቃሴ ሪፖርት ለክልሉ ንግ/ኢ/ት/ስ/ከ/ል/ማስ/ቢሮ እና ለቦርዱ ያቀርባል።

አንቀጽ ፲፪· <u>የኢንቨስትመንት ጽ/ቤት ሥልጣንና ተግባር</u>

፩· የክልሉን የኢንቨስትመንት ጉዳዮች ይመራል እንቅስቃሴውንም ያበረታታል ያስተባብራል ያስፋፋል።

፪· ምቹ የኢንቨስትመንት ሁኔታዎችን ለመፍጠር ሊወሰዱ የሚገቡ የፖሊሲና የአፈጻጸም እርምጃ ዎችን ያመነጫል ለቦርድ ያቀርባል ሲፈቅድም ተግባራዊነቱን ይከታተላል።

፫· የክልሉን የሀብት ክምችትና የኢንቨስትመንት አዲስ መረጃዎችን ይሰበስባል ያገናኛል ይተነ ትናል ያሰራጫል ተጨባጭ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችን ያስተዋውቃል በግብርና፣ በኢንዱ ስትሪ፣ በኮንስትራክሽን፣ በመንገድና ትራንስ ፖርት።

፬· የክልሉን ኢንቨስትመንት ለማበረታታት ይህንን አዋጅ ተደግፎ ለአፈጻጸሙ ደንብና መመሪያ በማዘጋጀት ደንቡ በክልሉ መንግሥት መስተ ዳድር ም/ቤት ቀርቦ እንዲጸድቅ ለቦርድ ያቀርባል። የኢ.ፌ/ዲ/ሪ/መ/የኢንቨስትመንት ኮሚሽን ደንብና መመሪያዎችን ያስፈጽማል።

፭· ኢንቨስትመንት ለማበረታታት የሚጠቅሙ ኤግ ዚቢሽኖች፣ ስብሰባዎች፣ ሥልጠናዎች ሴሚናሮች የመሳሰሉትን እንደ አግባቡ በክልሉ ያካሂዳል ለባለሃብቶች የምክር ድጋፍ ይሰጣል።

፮· ኢንቨስትመንት ለማስፋፋት በባለሀብቶችና በመ ንግሥታዊ መ/ቤቶች በመስተዳድሮችና በሌሎች ኢንቨስትመንትን በተመለከተ አግባብነት ባላቸው መካከል ግንኙነት እንዲኖር ያደርጋል።

፯· ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋት የሚረዱ ጽሁፎችን መግለጫዎችን ፊልሞችንና የመሳሰ ሉትን በማዘጋጀትና በማሰራጨት የማስተዋወቅ ሥራ ይሰራል።

፰· ከባለሀብቶች የሚቀርቡ የኢንቨስትመንት ፍቃድ ማመልከቻ በዚህ አዋጅና አዋጁን ለማስ ፈጸም ከወጡት ደንቦችና መመሪያዎች አንጻር በመመርመር ለክልሉ ልማት ይጠቅማል ለሚለው የኢንቨስትመንት ፍቃድ በተጠየቀ በ፭ ቀናት ውስጥ ይሰጣል የማበረታቻ ጥያቄዎች ይወስናል።

፱· የኢንቨስትመንት ፍቃድ የሰጣቸውን ባለሃብቶች ኢንቨስትመንት ፍቃድ የያዛቸውን ግዴታዎችና ሁኔታዎች መከበራቸውን ያረጋግጣል ፍቃዶ ችንም መዝግቦ ይይዛል።

፲· በዞንና በወረዳ ሪፖርቶችን ያሰባስባል ለቦርድ ያቀርባል።

፲፩· የጽ/ቤቱን ንብረት በጥንቃቄ ይይዛል።

፲፪· በኢንቨስትመንት ላይ የሚያጋጥሙ ችግሮችን ይለያል ከነመፍትሄ ሀሳቡም ለቦርድ ያቀርባል።

፲፫· ለክልሉና ለኅብረተሰቡ ጠቃሚ ያልሆኑትን የኢን ቨስትመንት ማመልከቻ ጥያቄም ይከላከላል ይቆ ጣጠራል።

፲፬· በክልሉ ኢንቨስትመንት ቦርድ መሬት እንዲሰ ጣቸው ለተፈቀዱ ፕሮጀክቶች መሬት ይሰጣል።

፲፭· ሌሎች ከበላይ አካላት የሚሰጡትን ተመሳሳይ ተግባሮችን ያከናውናል።

11. *Powers and Duties of the Head of the Investment Offices*

1) to decide on ways of implementation of matters provided for in this proclamation and related matters and ensure their implementation.
2) to create conducive atmosphere for the implementation of the powers and duties of the office mentioned under Art. 12 of this Proclamation.
3) to prepare and submit to the Regional State Council the work programme and budget of the Office and implement upon approval;
4) to effect expenditure in accordance with the budget approved for the office and employ the necessary staff in accordance with the law;
5) submit report of the office to the regional Trade Industry, Transport Works Urban Development Coordination Bureau and to the Board.

12. *Powers and Duties of the Office*

The Office shall have the following powers and duties:

1) direct investment matters of the Region and promote, coordinate and enhance activities theron;
2) to initiate and submit to the Board policy and implementation measures needed to create a conducive investment climate and follow up their implementation upon approval;
3) collect, compile, analyze and disseminate information on the resource potential of the Region and on the investment opportunities it offers; promote concrete investment projects especially in areas of agriculture, industry, construction and transportation;
4) issue regulations and directives on the basis of this Proclamation so as to promote investment in the Region; cause the implementation of regulaltions and directives issued by the Investment Authority of the Federal Government;
5) organize and conduct, with a view to promote investment, such activities as exhibition, conference, training, seminars and the like in the Region or other parts of the country as may be appropriate, give advisory support to investors;
6) realize liaison between investors, public offices, other Regional governments and other relevant organs, with a view to enhancing investment;
7) prepare and distribute pamphlets, brochures; films, and other materials that help to enhance investment;
8) issue investment, permits to investments seemed beneficial to the development of the Region within 5 days of receipt of an application for investment permit after due examination and investigation into project proposals and project profiles submitted by investors and decide on applications for incentives
9) monitor the implementation of investment projects for which it has issued permits; ensure that the terms and conditions of the investment permits are compiled with and keep a record of permits;
10) gather reports from Zones and Woredas and submit same to the Board;
11) maintain with care the properties of the Office;
12) identify problems related to investment and submit; to the Board with possible solutions;
13) refuse and control issuance of permits for investment applications repugnant to the laws of the Region and its people
14) to allocate land to an investment project approved by the Board;
15) carry out such other duties given to it by a superior organ,

**አንቀጽ ፲፫· የገቢ ምንጭ**

ጽ/ቤቱ ከዚህ ቀጥሎ የተዘረዘሩት የገቢ ምንጮች ይኖሩታል

፩· ክልል ም/ቤት በበጀት መደብ የሚሰጠው ገንዘብ
፪· ከሚሰበስበው የአገልግሎት ክፍያ
፫· ከማንኛውም ሌላ ምንጭ የሚገኝ ገቢ እርዳታና ስጦታ

**አንቀጽ ፲፬· የሂሳብ መዛግብት**

፩· የጽ/ቤቱ ተገቢ የሆነ የሂሳብ መዛግብትና ሰነዶችን ይጠብቃል።
፪· የጽ/ቤቱ የሂሳብ መዛግብትና ሰነዶች ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ በክልሉ ዋና ኦዲተር ይመረመራሉ።

**ንኡስ ክፍል ሦስት**
**ስለ ዞን ኢንቨስትመንት ኮሚቴ መቋቋም**

**አንቀጽ ፲፭· የዞን ኢንቨስትመንት ኮሚቴ ስለማቋቋም**

፩· በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በዚህ አዋጅ መሰረት የኢንቨስትመንት ኮሚቴ በዞን ደረጃ ይቋቋማል።
፪· የዞን ኢንቨስትመንት ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለቦርድ ሲሆን የዞን ም/ቤት መስተዳድር ለኢንቨስትመንት ኮሚቴ አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል።

**አንቀጽ ፲፮· የዞን ኢንቨስትመንት ኮሚቴ አባላት**

፩· የዞን መስተዳድር ዋና አስተዳዳሪ ………. ሰብሳቢ
፪· የዞን ኢንቨስትመንት ዴስክ ………. ጸሐፊና አባል
፫· የዞን ንግድ ኢ/ት/ክ/ልማት ማስተባበሪያ ቢሮ ኃላፊ …….. አባል
፬· የዞን አርብቶ አደር ገጠር ልማት ማስተባበሪያ ቢሮ ………”
፭· የፋይናንስ ኢኮኖሚ ልማት ማስተባበሪያ ቢሮ ……………… ”
፮· እንስሳትና እርሻ ልማት ዴስክ ……………… ”
፯· ንግድ ኢ/ት/ዲስክ …………………………”
፰· ሥራና ከተማ ልማት ዲስክ ………………….. ”

**አንቀጽ ፲፯· የዞን ኢንቨስትመንት ኮሚቴ ሥልጣንና ተግባር**

፩· የኢንቨስትመንት አዋጅ በሚደነግገው መሰረት የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴዎችንና ተግባራዊነታቸውን በቅርብ ይቆጣጠራል ለባለሀብቶች አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል።
፪· በሥሩ የሚገኙትን ወረዳዎች የኢንቨስትመንት ሪፖርት ያጠናቅራል ለጽ/ቤቱና ለቦርድ ያቀርባል።
፫· በቦርድና በክልሉ ኢንቨስትመንት ጽ/ቤት የተላለፉትን የኢንቨስትመንት ፖሊሲዎች መመሪያዎች ተግባራዊ ያደርጋል የዞን ኢንቨስትመንት ኮሚቴ ለኢንቨስትመንት ተግባር የሚውል መሬት በመመደብና የመደቧቸውን መሬት የሚመለከት መረጃዎችን ለኢንቨስትመንት ቦርድ ያስተላልፋል።

**ንኡስ ክፍል አራት**
**ስለወረዳ ኢንቨስትመንት ኮሚቴ መቋቋም**

**አንቀጽ ፲፰· የወረዳ ኢንቨስትመንት ኮሚቴ መቋቋም**

፩· በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የኢንቨስትመንት ኮሚቴ በወረዳ ደረጃ ይቋቋማል
፪· የወረዳ ኢንቨስትመንት ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለዞን ኢንቨስትመንት ኮሚቴ ሲሆን የወረዳ መስተዳድር ም/ቤት ለኢንቨስትመንት ኮሚቴ አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል።

13. *Source of Fund*

The Office shall have its funds drawn from the following sources:

1) The budgetary allocations made by the state Council;
2) service fees collected by it;
3) income, assistance and grants obtained from any other source;

14. *Books of Account*

1) The Office shall keep complete and accurate books of account and financial documents;
2) The books of accounts and documents of the Office shall be audited; annually by the Chief Auditor of the Region.

*SUB SECTION THREE*
*Zonal Investment Committee*

15. *Establishment of Zonal Investment Committee*

1) In the Afar National Regional State an Investment Committee shall be established at Zonal Administration level.
2) The Zonal Investment Committee shall be accountable to the Board. The Zonal Administration Council shall give the necessary support to the Investment Committee.

16. *Members of the Zonal Investment Committee*

1) Chief Administrator of the Zonal Administration ....................................Chairperson.
2) Zonal Investment Desk ........................... Member.
3) Head of the Trade Industry Transport Public Work & Urban Development Bureau ,,
4) Zonal Pastoralist Rural Development Coordinator Bureau .................................... ,,
5) Finance and Economic Development Bureau ........................................................ ,,
6) Animal & Agricultural Development Bureau ........................................................ ,,
7) Trade Industry & Transport Desk ............... ,,
8) Public Work & Urban Development............ ,,

17. *Powers and Duties of the Zonal Investment Committee*

The Zonal Investment Committee shall have the following powers and duties to:

1) Supervise closely, within its own respective zone, the implementation of investment activities in conformity with this Proclamation;
2) Consolidate and submit to the Office investmen reports of all woredas within the the respective zone
3) Implement the investment policies and directive issued by the Board and the Office. The Zona Investment Committee allocates land for investmen activities and transmits information on suc allocations to the investment Board.

*SUB SECTION FOUR*
*Woreda Investment Committee*

18. *Establishment of Woreda Investment Committee*

1) In the Afar National Regional State an Investmer committee shall be established at the Woreda level
2) The Woreda Investment Committee shall be accour table to Zonal Investment Committee. The Wored Administration Council shall give the necessar support to the investment Committee.

አንቀጽ ፲፱· የወረዳ ኢንቨስትመንት ኮሚቴ አባላት

፩· የወረዳ መስተዳድር ም/ቤት አስተዳዳሪ ............. ሰብሳቢ

፪· የወረዳ አርብቶ አደር ገጠር ልማት ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ........ አባል

፫· የወረዳ እንስሳት እርሻ ልማት ጽ/ቤት ኃላፊ .................... ››

፬· የወረዳ ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ማ/ጽ/ቤት ኃላፊ .......... ››

አንቀጽ ፳· የወረዳ ኢንቨስትመንት ኮሚቴ ሥልጣንና ኃላፊነት

፩· በኢንቨስትመንት አዋጅ በተደነገገው መሠረት የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴዎችን ተግባራዊነት ይቆጣጠራል ለኢንቨስትመንት አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል።

፪· ከሚመለከታቸው አካል ጋር በመተባበር የኢንቨስትመንት ክፍሎችንና ለልማት የሚውሉ አካባቢዎችን ይከልላል ጥናት ያካሂዳል የተከለሉ ሥፍራዎችን በስፋትና በመጠን ለይቶ ለዞኑ ኮሚቴ ያቀርባል።

፫· ለዞን ኢንቨስትመንት ኮሚቴ የወረዳውን የሥራ እንቅስቃሴ ሪፖርት ያቀርባል።

፬· የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴን በተመለከተ አስተማማኝ መረጃዎችን ለዞን ኢንቨስትመንት ኮሚቴ ያቀርባል።

፭· ከሚመለከታቸው አካል ስለኢንቨስትመንት የሚሰጡትን መመሪያዎችና ውሳኔዎች ያስፈጽማል።

፮· የሚሰጡትን ሌሎች ተመሳሳይ ተግባራትን ያከናውናል።

አንቀጽ ፳፩· የዞንና የወረዳ ኢንቨስትመንት ኮሚቴ ስብሰባዎች

፩· የዞንና የወረዳ ኢንቨስትመንት ኮሚቴ ቢያንስ በወር አንድ ግዜ መሰብሰብ ይኖርባቸዋል።

፪· አብዛኛው የኮሚቴ አባላት በስብሰባው ላይ ከተገኙ ምልአተ ጉባኤው እንደተሟላ ተቆጥሮ ሰብሰባውን ማካሄድ ይችላሉ።

፫· ማንኛውም ስብሰባ ላይ ውሳኔዎች በድምጽ ብልጫ መሰረት ይሆናል ድምጽ እኩል በእኩል ከሆነ ሊቀመንበሩ /ሰብሳቢው/ ወሳኝ የሆነ አብላጫ ድምጽ ይኖረዋል።

፬· ኮሚቴው በሚያደርጋቸው ስብሰባዎች ላይ አማካሪዎች ያለድምጽ እንዲገኙ ሊያደርግ ይችላል።

## ክፍል አራት
## ስለ ኢንቨስትመንት ፈቃድ

አንቀጽ ፳፪ ለኢንቨስትመንት ፍቃድ ስለሚቀርብ ማመልከቻ

የኢንቨስትመንት ፍቃድ ለማግኘት የሚፈልግ ባለሀብት ለዚሁ ተግባር የተዘጋጀውን የማመልከቻ ቅጽ በመሙላት ከሚከተሉት ሰነዶች ጋር በአንድ ቅጅ (ኮፒ) አግባብ ላለው ለኢንቨስትመንት መሥሪያ ቤት ማቅረብ አለበት ፡፡

ሀ) ማመልቻው የተፈረመው በወኪል ከሆነ የውክልና ሥልጣን ማረጋገጫ ሰነድ ፎቶ ኮፒ ፡፡

ለ) ኢንቨስትመንቱ የሚካሄደው በግለሰብ ከሆነ የባለሃብቱ የመታወቂያ ካርድ ፎቶኮፒ ወይም የሀገር ውስጥ ባለሃብትነት ሰርትፊኬት ፎቶ ኮፒ እና ሁለት የቅርብ ጊዜ ጉርድ ፎቶ ግራፎች ፡፡

ሐ) ኢንቨስትመንቱ የንግድ ማኅበር ከሆነ የማኅበሩ የመመስረቻ ጽሁፍና የመተዳደሪያ ደንብ ፎቶ ኮፒ ወይም ማኅበሩ አዲስ የሚቋቋም ከሆነ ከዚህ በተጨማሪ የማኅበርተኞቹ የመታወቂያ ካርድ ፎቶ ኮፒ ወይም የሀገር ውስጥ ባለሃብትነት ሰርትፊኬት ፎቶ ኮፒ ፡፡

19. *Members of the Woreda Investment Committee*

1) Administrator of the Woreda Administration Committee ............................................... Chairperson.
2) Woreda Pastoralist Rural Development Coordinator Office ................................ Member.
3) Head of Animal Agricultural Development Office of the Woreda.................................. ''
4) Head of Finance & Economic Development Coordinator Office ..................................... ''

20. *Powers and Duties of the Woreda Investment Committee*

The Woreda Investment Committee shall have the following powers and duties to:

1) See to it that investment activities are carried out in compliance with this Proclamation; give the necessary support and assistance to investors;
2) Stake out or appropriate, in cooperation with the appropriate authorities; plots of lands for investment and development activities and undertake research thereon and submit to the respective zonal investment committee plots thus staked out according to their area and size;
3) submit its operational reports to the respective Zonal Investment Committee;
4) submit accurate and reliable information pertaining to investment activities in the woreda to the Zonal Investment Committee;
5) execute directives and decisions issued concerning investments by the appropriate authorities;
6) carry out such other duties given to it

21. *Meetings to Zonal & Woreda Investment Committee*

1) Zonal as well as Woreda Investment Committees shall hold a meeting at least once in a month.
2) There shall be a quorum where more than half of the members are present at a meeting.
3) Decisions of each Committee shall be passed by a majority vote; and incase of a tie; however, the chairman shall have a casting vote.
4) A committee may invite counselors to attend its meetings.

## *SECTION FOUR*
## *Investment Permit*

22. *Applications for Investment Permit*

An application for investment permit shall be made in a form designed for such purpose and submitted to the Office together with the following information:

(a) power of attorney in the case of an application made through an agent;
(b) in case of sole proprietorship, photocopy of the identity card or photocopy of domestic investment and two passport size photographs.
(c) in the case of a business organization the Memorandum and Articles of association;

የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት

# የአፋር ክልል ነጋሪት ጋዜጣ
# AFAR REGION NEGARIT GAZETA
## OF THE AFAR NATIONAL REGIONAL STATE

ሰባተኛ ዓመት ቁጥር —
ሠመራ ሰኔ ፴ ቀን ፲፱፻፺፬ ዓ/ም

በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት
ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

7th Year No. ....
SEMERA – 7th July 2002

ማውጫ

የአፋር ብሔራዊ ክልል መንግሥት የአፋር ቋንቋ ጥናትና ማበልጸጊያ ማዕከል አዋጅ ቁጥር ፲፰/፲፱፻፺፬ ............. ገጽ ፩

CONTENTS

Proclamation No. 18/2002
The Afar Regional State Afar languge Research and development proclamation No. 18/2002 Page 1

አዋጅ ቁጥር ፲፰/፲፱፻፺፬
በአፋር ብሔራዊ ክልል መንግሥት ም/ቤት
ጠባቂነት የወጣ የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት
የአፋር ቋንቋ ጥናትና ማበልጸጊያ ማዕከል ለማቋቋም
የወጣ አዋጅ

የአፋር ብሔራዊ ክልል ራሱን የቻለ የክልል መንግሥት ሆኖ በህገ መንግሥት መቋቋሙ የሚታወቅ ሲሆን ክልሉን ብሔራዊ ክልል ከሚያሰኙት መለኪያዎች አንዱ የራሱ ቋንቋ መናገሩ ነው ። የአፋር ቋንቋ የክልሉ የሥራ ቋንቋ ሆኖ እንዲወጣ በጽሑፍ ቋንቋነቱ ዳብሮ መገኘት አለበት ። ይህንን ብሔራዊና አጣዳፊ ጉዳይን ከግቡ ለማድረስ እንዲቻል አንድ የተሟላ የአፋርኛ ቋንቋ የጥናትና ማበልጸጊያ ማዕከል ማቋቋም አስፈልጓል ።

በመሆኑም በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ም/ቤት ተሻሽሎ በወጣው የክልሉ ሕገ–መንግሥት አንቀጽ ፵፯ ንዑስ አንቀጽ ፫ (ሀ) መሠረት የሚከተለው ታውጇል ።

ክፍል አንድ
ጠቅላላ ድንጋጌ

አንቀጽ ፩
አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ የአፋር ቋንቋ ጥናትና ማበልጸጊያ ማዕከል ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፲፰/፲፱፻፺፬ ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ።

አንቀጽ ፪
ትርጓሜ

፩· "ክልል" ማለት የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ማለት ነው ፤
፪· "ቦርድ" ማለት የአፋር ቋንቋ ጥናትና ማበልጸጊያ ማዕከል ቦርድ ማለት ነው ፤
፫· "ማዕከል" ማለት የአፋር ቋንቋ ጥናትና ማበልጸጊያ ማዕከል ማለት ነው ፤

PROCLAMATION NO.18/2002

*A PROCLAMATION TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF AFAR LANGUAGE RESEARCH AND DEVELOPMENT CENTER*

WHEREAS, it is known that Afar National Region has been formed as an independent Regional State. Its language is one of the criteria for the formation of Such National Region. The language of Afar should be developed in writing septem in order to become the official language of the Region. Therefore, it has become necessary to establish Afar Language Research and Development Center to implement realize such urgent matter.

NOW, THERFORE, in accordance with Article 47 Sub-Article 3 (A) of the Revised constitution of Afar National Regional State hereby proclaimed as follows:

PART ONE
*General Provision*

*Article 1*
*Short Title*

This proclamation may be cited as ''Afar language Research and Development Center Proclamation No. 18 2002''.

*Article 2*
*Definitions*

In this proclamation:-

1. ''Region'' means the Afar National Regional State;
2. ''Board'' means the Board for Afar Language Research and Development Center;
3. ''Centre'' means Afar language Research and development center.

ያንዱ ዋጋ 7·25
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ·ሣ·ቁ· ፵
Negarit Gazeta P.O.Box 40

ክፍል ሁለት

፫
ሉ መቋቋም
የአፋር ቋንቋ ጥናትና ማበልጸጊያ ማዕከል ከዚህ በኋላ ማዕከሉ እየተባለ የሚጠራ የሕግ ሰውነት ያለው ራሱን የቻለ የክልል መንግሥት መስሪያ ቤት ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል ።

፬
ሉ ተጠሪነት
ሉ ተጠሪነት ለቦርድና ለክልሉ አቅም ግንባታ ማስተባበሪያ ሆናል ፤

፭
ሉ ዋና ጽ/ቤት
ሉ ዋና ጽ/ቤት በሰመራ ሆኖ እንደየአስፈላጊነቱ በየዞኖችና ዳዎች ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ሊኖሩት ይችላል።

፮

ሉ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል ፤
. የአፋር ቋንቋ የክልሉ የሥራ ቋንቋ ሆኖ እንዲያገለግል ማሳደግና ማስፋፋት ፤
. በአፋርኛ ቋንቋ ባዕድ የሆኑ ቃላቶች ፣ ፅንሰ-ሐሳቦችና ተርሚኖሎጂስ በአንድ ወጥነት (Standardization) መጠቀም የሚያስችል ምቹ መንገድን ይፈጥራል ፤
. ከሚመለከታቸው መንግሥታዊ አካላት ጋር በመተባበር የክልሉ ሕብረተሰብ በአፍ መፍቻ ቋንቋው የመማር መብቱ ተግባራዊ እንዲሆን ያላሰለሰ ጥረት ያደርጋል ። የመጀመሪያ ሳይክል የትምህርት መፃሕፍት ዝግጅት ላይ የበኩሉን ድርሻ በከፍተኛ ሁኔታ ይወጣል ፤
፬. ከክልሉ መንግሥት መስተዳድር አካላት በሚያገኘው ድጋፍ በመታገዝ ቋንቋን የማስተማር ሂደት እንዲፋጠን ያደርጋል ፤
፭. ልዩ ልዩ ፕሮግራሞችን በመንደፍ የክልሉ ነዋሪ የሆኑ የሕብረተሰብ ክፍሎች ቋንቋውን እንዲያነቡና እንዲጽፉ ያስተምራል ፤
፮. የአፋር ቋንቋን ሥረ-መሠረት ምርምርና ጥናቶችን ያካሂዳል ያሰባስባል ያሳትማል ፣ ያሰራጫል ፤
፯. በክልሉ መንግሥት የሚወጡ ልዩ ልዩ አዋጆች ደንቦችና መመሪያዎች ወደ አፋርኛ ቋንቋ እንዲተረጎም ጥያቄ ሲቀርብለት የትርጉም ሥራዎችን ያከናውናል ፤

ጽ ፯
ከሉ ሥልጣንና ተግባር
፩. የማዕከሉ የአፋር ቋንቋ እንዲበለጽግ ልዩ ልዩ የአፃፃፍ ስልቶችን ይነድፋል ፣ የክልሉ የሥራ ቋንቋ ሆኖ ወደ ተግባር እንዲሸጋገር ጥረት ያደርጋል ፤
፪. የየአካባቢ አነጋገሮችና አባባሎች መሠረታቸውን ሳይስቱ ለተሻለ ግልጋሎት እንዲውሉ ያደርጋል ፤
፫. አዳዲስ ጽንሰ ሀሳቦች የሚወክሉና የቴክኖሎጂ ቃላትን የሚተረጉሙ አዳዲስ ቃላትን መፍጠርና ማሰራጨት የመሳሰሉትን ይሠራል ፤
፬. ድምጾችን በሚወክሉና በሆሄዎች ላይ የሚጨመሩና የሚቀነሱ ምልክቶችን በጥናት በሥራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል ፤
፭. የአፋር መዝገበ ቃላትን ያዘጋጃል ፣ አሳትሞ ያሠራጫል ፣
፮. ልዩ ልዩ የቋንቋና የታሪክ መጽሐፍትን ያሰባስባል ፤
፯. ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የአንደኛ ደረጃና የጎልማሶች ትምህርት መማሪያ ካረክለም ያዘጋጃል ፤
፰. ልዩ ልዩ የቋንቋ ኮርሶችን ያዘጋጃል ያስተምራል ፤
፱. የአፋርኛ ቋንቋና የታሪክ ጥናት ምርምር ሥራዎችን ያከናውናል መረጃዎችን ያሰባስባል ፣ ለሚመለከታቸው ያሰራጫል ፤

PART TWO

*Establishment of the Center*

Article 3

*Establishment*

The Afar Language Research and Development Center the ''Center'' hereinafter is established as an autonomous office of the Regional State having its own legal personality.

Article 4

*Accountability*

The Center shall be accountable to the Board and capacity Building Coordination Bureau of the Region.

Article 5

*Head Office*

The Head Office of the Center shall be in Semera and it may have branch offices at zones and woredas as may be necessary.

Article 6

*Objectives*

The Center shall:-

1) develop and promoate the Afar language to become the official language of the Region;
2) create a conducive condition that enables to use borrowed words, concepts and terminologies in Afar language by standardizing them;
3) make in cooperation with the concerned government organs, intensive effort that the right of the society of the Region to learn in its mother tonque be realized; play
4) accelearte the teaching process of the language with the support it obtains from the Region's administrative organs;
5) teach various groups of the society how to read and write the language by devising different programmes;
6) conduct collect, publish and disseminate research and studies on the origin of the Afar language;
7) under take translation of proclamations, regulations and directivies issued by the Regional state into the Afar language.

Article 7

*Powers and Duties of the Center*

The Center Shall:

1) adapt different writing styles to develop the language; make efforts that the language be used as the official language of the Region;
2) adapt dialects and expressions for a better use without distorting
3) create and disseminate new words that express new concepts and technological ideas;
4) conduct study on the diacritics that are added to, or removed from the letters, that represent sounds, and implement it;
5) prepare, publish and disseminate dictionary in the Afar language;
6) gather various language and history books;
7) develop curriculum for primary and adult education in Cooperation with the concerned bodies;
8) organize and teach different language courses;
9) undertake studies and research on the Afar language and history; collect information and disseminate some to the concerned bodies;

## ክፍል ሁለት

አንቀጽ ፫
የማዕከሉ መቋቋም

፩· የአፋር ቋንቋ ጥናትና ማበልጸጊያ ማዕከል ከዚህ በኋላ ማዕከሉ እየተባለ የሚጠራ የሕግ ሰውነት ያለው ራሱን የቻለ የክልል መንግሥት መስሪያ ቤት ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል ።

አንቀጽ ፬
የማዕከሉ ተጠሪነት

የማዕከሉ ተጠሪነት ለቦርድና ለክልሉ አቅም ግንባታ ማስተባበሪያ ቢሮ ይሆናል ፤

አንቀጽ ፭
የማዕከሉ ዋና ጽ/ቤት

የማዕከሉ ዋና ጽ/ቤት በሰመራ ሆኖ እንደየአስፈላጊነቱ በየዞኖችና በወረዳዎች ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ሊኖሩት ይችላል።

አንቀጽ ፮
ዓላማ

ማዕከሉ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል ፤

፩· የአፋር ቋንቋ የክልሉ የሥራ ቋንቋ ሆኖ እንዲያገለግል ማሳደግና ማስፋፋት ፤
፪· በአፋርኛ ቋንቋ ባዕድ የሆኑ ቃላቶች ፣ ፅንሰ–ሐሳቦችና ተርሚኖሎጂስ በአንድ ወጥነት (Standardization) መጠቀም የሚያስችል ምቹ መንገድን ይፈጥራል ፤
፫· ከሚመለከታቸው መንግሥታዊ አካላት ጋር በመተባበር የክልሉ ሕብረተሰብ በአፍ መፍቻ ቋንቋው የመማር መብቱ ተግባራዊ እንዲሆን ያላሰለሰ ጥረት ያደርጋል ። የመጀመሪያ ሳይክል የትምህርት መፃሕፍት ዝግጅት ላይ የበኩሉን ድርሻ በከፍተኛ ሁኔታ ይወጣል ፤
፬· ከክልሉ መንግሥት መስተዳድር አካላት በሚያገኘው ድጋፍ በመታገዝ ቋንቋን የማስተማር ሂደት እንዲፋጠን ያደርጋል ፤
፭· ልዩ ልዩ ፕሮግራሞችን በመንደፍ የክልሉ ነዋሪ የሆኑ የሕብረተሰብ ክፍሎች ቋንቋውን እንዲያነቡና እንዲጽፉ ያስተምራል ፤
፮· የአፋር ቋንቋን ሥረ–መሠረት ምርምርና ጥናቶችን ያካሂዳል ያሰባስባል ያሳትማል ፣ ያሰራጫል ፤
፯· በክልሉ መንግሥት የሚወጡ ልዩ ልዩ አዋጆች ደንቦችና መመሪያዎች ወደ አፋርኛ ቋንቋ እንዲተረጎም ጥያቄ ሲቀርብለት የትርጉም ሥራዎችን ያከናውናል ፤

አንቀጽ ፯
የማዕከሉ ሥልጣንና ተግባር

፩· የማዕከሉ የአፋር ቋንቋ እንዲበለጽግ ልዩ ልዩ የአፃፃፍ ስልቶችን ይነድፋል ፣ የክልሉ የሥራ ቋንቋ ሆኖ ወደ ተግባር እንዲሸጋገር ጥረት ያደርጋል ፤
፪· የየአካባቢ አነጋገሮችና አባባሎች መሠረታቸውን ሳይስቱ ለተሻለ ግልጋሎት እንዲውሉ ያደርጋል ፤
፫· አዳዲስ ጽንስ ሀሳቦች የሚወክሉና የቴክኖሎጂ ቃላትን የሚተረጉሙ አዳዲስ ቃላትን መፍጠርና ማሰራጨት የመሳሰሉትን ይሠራል ፤
፬· ድምጾችን በሚወክሉና በሆሄዎች ላይ የሚጨመሩና የሚቀነሱ ምልክቶችን በጥናት በሥራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል ፤
፭· የአፋር መዝገበ ቃላትን ያዘጋጃል ፣ አሳትሞ ያሠራጫል ፣
፮· ልዩ ልዩ የቋንቋና የታሪክ መጽሐፍትን ያሰባስባል ፤
፯· ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የአንደኛ ደረጃና የጎልማሶች ትምህርት መማሪያ ካረክለም ያዘጋጃል ፤
፰· ልዩ ልዩ የቋንቋ ኮርሶችን ያዘጋጃል ያስተምራል ፤
፱· የአፋርኛ ቋንቋና የታሪክ ጥናት ምርምር ሥራዎችን ያከናውናል መረጃዎችን ያሰባስባል ፣ ለሚመለከታቸው ያሰራጫል ፤

## PART TWO
*Establishment of the Center*

Article 3
*Establishment*

The Afar Language Research and Development Center the ''Center'' hereinafter is established as an autonomous office of the Regional State having its own legal personality.

Article 4
*Accountability*

The Center shall be accountable to the Board and capacity Building Coordination Bureau of the Region.

Article 5
*Head Office*

The Head Office of the Center shall be in Semera and it may have branch offices at zones and woredas as may be necessary.

Article 6
*Objectives*

The Center shall:-

1) develop and promoate the Afar language to become the official language of the Region;
2) create a conducive condition that enables to use borrowed words, concepts and terminologies in Afar language by standardizing them;
3) make in cooperation with the concerned government organs, intensive effort that the right of the society of the Region to learn in its mother tonque be realized; play
4) accelearte the teaching process of the language with the support it obtains from the Region's administrative organs;
5) teach various groups of the society how to read and write the language by devising different programmes;
6) conduct collect, publish and disseminate research and studies on the origin of the Afar language;
7) under take translation of proclamations, regulations and directivies issued by the Regional state into the Afar language.

Article 7
*Powers and Duties of the Center*

The Center Shall:

1) adapt different writing styles to develop the language; make efforts that the language be used as the official language of the Region;
2) adapt dialects and expressions for a better use without distorting
3) create and disseminate new words that express new concepts and technological ideas;
4) conduct study on the diacritics that are added to, or removed from the letters, that represent sounds, and implement it;
5) prepare, publish and disseminate dictionary in the Afar language;
6) gather various language and history books;
7) develop curriculum for primary and adult education in Cooperation with the concerned bodies;
8) organize and teach different language courses;
9) undertake studies and research on the Afar language and history; collect information and disseminate some to the concerned bodies;

፲· በሥሩ ለሚገኙ ባለሙያዎች ለጥናትና ምርምር ሥራው በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ አገር የስልጠና ዕድል እንዲያገኙ ያደርጋል ፤

፲፩· ከልዩ ልዩ ቋንቋዎች ወደ አዳርኛ እንዲሁም በተቃራኒው ከአፋርኛ ወደ ሌሎች ቋንቋዎች የትምህርትና የሌሎች መጽሐፍት የትርጉም ሥራዎች ያከናውናል ፤

፲፪· በክልሉ መንግሥት የሚወጡ ህጎችን ፣ አዋጆችን ፣ ደንቦችንና መመሪያዎችን ወደ አፋርኛ ቋንቋ እንዲተ ረጎሙ ጥያቄ ሲቀርብ የትርጉም ሥራዎችን ያከናውናል፤

፲፫· ለቋንቋው ዕድገት አስተዋጽኦ በጽሑፍም ሆነ በቃል የሚያበረክቱ ወገኖችን ያበረታታል ይሸልማል ፤

## ክፍል ሦስት
## የቦርዱ አቋም

### አንቀጽ ፰
### የቦርድ አባላት

ቦርዱ ሰብሳቢውን ጨምሮ አግባብነት ያላቸውን ቢሮዎች የሚወ ክሉና በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት የሚሰየሙ አባላት ይኖሩታል ።

### አንቀጽ ፱
### የቦርዱ ተጠሪነት

የቦርዱ ተጠሪነት ለክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ይሆናል ።

### አንቀጽ ፲
### የቦርዱ ሥልጣንና ተግባር

ቦርዱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል ።

፩· በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፭ ላይ የተዘረዘሩት የማዕከሉ ዓላማዎችን ያስፈጽማል ፤

፪· በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፮ ላይ የተዘረዘሩትን የማዕከሉን ሥልጣንና ተግባር በበላይነት ይመራል ፣ የአዋጁን አፈፃፀም በበላይነት ይቆጣጠራል ፣ ይከታተላል ፤

፫· የማዕከሉ ሠራተኞች የሚተዳደሩበትን ውስጠ ደንብ (መመሪያ) ያፀድቃል ፤

፬· እንደ አስፈላጊነቱ የቴክኒክ አማካሪ ኮሚቴ ያቋቁማል ፣ አባላትንም ይመርጣል ፤

፭· የዓመቱን በጀትና የሥራ ዕቅድ ያፀድቃል ፤

፮· በሌሎች አስፈላጊ በሆኑ የማዕከሉ ጉዳዮች ውሳኔ ይሰጣል፤

### አንቀጽ ፲፩
### የቦርዱ ስብሰባ

፩· የቦርዱ ስብሰባ በየ፮ ወሩ በዓመት ሁለት ጊዜ የሚከናወን ሲሆን እንደ አስፈላጊነቱ አስቸኳይ ስብሰባ በማንኛውም ጊዜ ሊደረግ ይችላል ፤

፪· በቦርዱ ስብሰባ ላይ ከግማሽ በላይ አባላት ከተገኙ ምልዓተ—ጉባኤ ይሆናል ፤

፫· የቦርዱ አባላት ውሳኔ በስብሰባው ከተገኙ አባላት አብላጫ ድምፅ ሲደገፍ ሆኖ ድምፁ እኩል በእኩል የተከፈለ ከሆነ ሰብሳቢው ወገን ድምር ይኖረዋል ።

### አንቀጽ ፲፪
### የማዕከሉ ሥራ አስኪያጅ ሥልጣንና ተግባር

የማዕከሉ ሥራ አስኪያጅ ተጠሪነቱ ለቦርድና ለክልሉ የአቅም ግንባታ ማስተባበሪያ ቢሮ ኃላፊ ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል ፤

፩· ሥራ አስኪያጁ የማዕከሉ ዋና ሥራ አስፈፃሚ በመሆን የማዕከሉን ሥራዎች በበላይነት ይመራል ፤

፪· ለማዕከሉ የተሰጠውን ስልጣንና ተግባር ሥራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል ፤

፫· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ እና ፪ የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ሥራ አስኪያጁ ፤

10) facilitate training opportunity on study and researc in the country and abroad for its experts;
11) translate of text books and other books from differen languages into Afar ianguage and vice versa;
12) translate of laws, proclamations, regulations an directives into Afar language upon request of th Regional State;
13) encourage and award individuals who contribute i writing as well as orally for the development of th language.

## PART THREE
## *Structure of the Board*

### *Article 8*
### *Board members*

The Board shall have members appointed by the Council o the Region and representing relevant bureaux including the Chairperson of the Board.

### *Article 9*
### *Accountability of the Board*

The Board shall be accountable to the Administrative Council of the Region.

### *Article10*
### *Powers and Duties of the Board*

The Board shall:

1) execute the objectives of the Center stated under Article (5) of this Proclamation;
2) Supervise the powers and duties of the Center detailed under Article (6) of this Proclamation; Supervise and follow up the implementation of the Proclamation;
3) approve internal regulations of the staff of the center;
4) establish, as may be necessary, technical advisory committee and elect members;
5) approve annual budget and work plan;
6) give decision on other necessary matters of the Center.

### *Article 11*
### *Meetings of the Board*

1) The meetings of the Board shall be held every 6 months and extraordinary meetings may be held at any time as may be necessary;
2) There shall be a quorum where more than half of the Board members are present at the meeting.
3) Decision of the Board members shall be passed by a majority vote; in case of a tie, the chairperson shall have a casting vote.

### *Article12*
### *Powers and Duties of the Center's manager*

The Manager of the Center shall be accountable to the Board and the Head of the capacity Building Coordination Bureau of the Region and shall have the following powers and duties:-

1) He is the chief Executive of the Center, direct overall activities of the Center;
2) He shall implement powers and duties given to the Center
3) without prejudice to Sub-Articles (1) and (2) of this Article, the manager shall:

ሀ) የማዕከሉን ዕቅድና የፋይናንስ አጠቃቀም ይቆጣጠራል ይከታተላል ፤

ለ) ቦርዱ በሚያፀድቀው መመሪያና አግባብ ባለው ሕግ መሠረት የማዕከሉን ሠራተኞች ይቀጥራል ፤ ያስተዳድራል ፤ ያሰናብታል ፤

ሐ) የማዕከሉን የሥራ ዕቅድና በጀት አዘጋጅቶና አጠናክሮ ለቦርድ ያቀርባል ፤ ሲፈቀድም በፀደቀው መሠረት በሥራ ላይ መዋሉን ይከታተላል ፤

መ) ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ሁሉ ማዕከሉን ይወክላል ፤

ሠ) የማዕከሉን የሥራ አፈፃፀምና የሂሣብ ሪፖርት አጠናክሮ ለቦርድ ያቀርባል ፤

ረ) የጥናት ፤ የስብሰባና የመሣሠሉ ከፍተኛ ወጭዎች ላይ ይወስናል ።

## ክፍል ሦስት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**አንቀጽ ፲፬**

**የበጀት ምንጭ**

የክልሉ መንግሥት የሚመደበውና ከሌሎች የሚገኝ ድጋፍ ይሆናል።

**አንቀጽ ፲፭**

**ስለ ሂሣብ መዛግብት**

፩· ማዕከሉ የተሟላና ትክክለኛ የሆኑ የሂሣብ መዛግብት በሚታቀፍበት ፑል ውስጥ ይኖሩታል ፤

፪· የማዕከሉ የሂሣብ መዛግብቶችና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በክልሉ ዋና ኦዲተር መ/ቤት ቀርበው በየዓመቱ ይመረመራል ።

**አንቀጽ ፲፮**

**ተፈፃሚነት የሌላቸው ሕጎች**

ማንኛውም ሌላ ሕግ ከዚህ አዋጅ ጋር ወይም በዚህ አዋጅ መሠረት ከሚወጡ ሕጎች ጋር የሚቃረኑ ከሆነ በአዋጁ ውስጥ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም ።

**አንቀጽ ፲፯**

**አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በአፋር ክልል ነጋሪት ጋዜጣ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ የፀና ይሆናል ።

ሰኔ ፴ ቀን ፲፱፻፺፬ ዓ.ም.

ሠመራ

እስማኤል አሊ ሲሮ
የአፋር ብ/ክ/መንግሥት
ርዕሰ መስተዳድር

(a) Supervise and follow up plan and financial usage of the center;

(b) Employ, administer and discharge employees of the Center in accordance with a directive approved by the Board and relevant law;

(c) Prepare and compile work plan and budget of the Center and present the same to the Board; and follow up its implementation upon approval;

(d) represent the Center in all its dealings with third parties;

(e) compile and submit performance and financial reports of the Center to the Board;

(f) decide on high expenses such as for research, and conference.

## PART THREE
## Miscellaneos Provision

**Article 14**

**Budget Source**

Budget source of the Center shall be that which shall be that which is allocated by the Regional Government and assistance obtained from other sources.

**Article 15**

*Books of Accounts*

1) The Center shall have complete and accurate books of accounts in its pools.
2) The Center's books of accounts and financial documents shall be audited annually by the Auditor General of the Region.

**Article 16**

*Inapplicable Laws*

Any other law inconsistent with this Proclamation or laws enacted in accordance with this Proclamation shall not apply to matters provided for herein.

**Article 17**

*Effective Date*

This Proclamation shall enter into force on the date of its publication in the Afar Region Negarit Gazeta.

7th July 2002
Semera

Ismael Ali Sero
Afar N.R. State President
Chief Administrator of Afar N.R. State

የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት

# የአፋር ክልል ነጋሪት ጋዜጣ
# AFAR REGION NEGARIT GAZETA

**OF THE AFAR NATIONAL REGIONAL STATE**

ሰባተኛ ዓመት ቁጥር ፫
ሠመራ ጥር ፳፱ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ/ም

በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት
ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

7[th] Year No. —
SEMERA – 7[th] January 2003


ማውጫ


አዋጅ ቁጥር ፲፱/፲፱፻፺፭ ዓ.ም
የአፋር ብሔራዊ ክልል መንግሥት የም/ቤት አባላት የመረጣቸው ህዝብ አመኔታ ባጣባቸው ጊዜ ስለሚወስደው እርምጃ የወጣ አዋጅ ..................................... ገጽ ፩


CONTENTS


Proclamation No. 19/2003
The "Action to be Taken against the Members of the Afar National Regional State Council upon Loss of Trust by the Electorate Proclamation ............ Page 1


የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የም/ቤት አባላት በመረጣቸው ህዝብ አመኔታ ባጣበት ጊዜ ስለሚወስደው እርምጃ፣ የወጣ አዋጅ ቁጥር ፲፱/፲፱፻፺፭፣

የአፋር ብሔራዊ ክልል መንግስት ህገ–መንግስት በአንቀጽ ፲፪ ስር ማንኛውም ኃላፊና የህዝብ ተመራጭ ኃላፊነቱን ሲያጓድል ተጠያቂ እንደሚሆን እና በማንኛውም የአፋር ብሔራዊ ክልል መንግስት ም/ቤት አባል በመረጠው ህዝብ አመኔታ ባጣበት ጊዜ የሚችል የሚደነግግ በመሆኑ፣

በዚህም መሠረት ይህ መሰረታዊ የተጠያቂነት ሕገ መንግሥታዊ መርህ ስራ ላይ እንዲውል የሚያስችል ህግ አስፈላጊና ወቅታዊ ሆኖ በመገኘቱ ፤

በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ም/ቤት ተሻሽሎ በወጣው የክልሉ የ፲፱፻፺፬ ዓ.ም ህገ–መንግሥት አንቀጽ ፵፯/፫/ሀ መሰረት የሚከተለው ታውጇል።

ክፍል አንድ
ጠቅላላ ድንጋጌ

አንቀጽ አንድ
አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ የአፋር ብሔራዊ ክልል መንግሥት የም/ቤት አባላት የመረጣቸው ህዝብ አመኔታ ባጣባቸው ጊዜ ስለሚወስደው እርምጃ የወጣ አዋጅ ቁጥር ፲፱/፲፱፻፺፭ ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

PROCLAMATION TO PROVIDE FOR THE ACTION TO BE TAKEN AGAINST THE MEMBERS OF THE AFAR NATIONAL REGIONAL STATE COUNCIL UPON lOSS OF TRUST BY THE ELECTORATE

WHEREAS, it is provided for in Article (12) of the Constitution of the Afar National Regional State that any deputy shall lose his mandate of representation in accordance with law upon loss of trust by electorate;

WHEREAS, it has become necessary to enact law that enables to implement this fundamental constitutional principle;

NOW,THEREFOR in accordance with article 47(3) (a) of the Revised Constitution of the Council of the Afar National Regional State, it is hereby proclaimed as follows:

*PART ONE*
*General Provision*

*Article 1.*

1. *Short Title*

This Proclamation may be cited as the "Action to be Taken against the Members of the Afar National Regional State Council upon Loss of Trust by the Electorate Proclamation No 19/2003


ያንዱ ዋጋ 5.30
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፵
Negarit G.P.O.Box 40

## ክፍል ሁለት

### አንቀጽ ሁለት

### ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፦

፩· "ተመራጭ" ማለት በኢትዮጵያ የምርጫ ቦርድ አፈፃፀም ህግ መሰረት አንድ አካባቢን ለመወከል የተመረጠና በምርጫ ቦርድ የምስክር ወረቀት የተሰጠው የም/ቤት አባል ነው።

፪· "የምርጫ አካባቢ" ማለት በምርጫ ህግ መሰረት የተወሰነ የህዝብ ብዛት የሚያካትት አካባቢና ልዩ የምርጫ አካባቢ ማለት ነው።

፫· "መራጭ" ማለት በምርጫ ህግ መሰረት እድሜው /ዋ/ አስራ ስምንት ዓመት የሞላው/ላት/ እና በምርጫ አካባቢው ከሁለት ዓመት በላይ የተመቀመጠ/ች/ ግለሰብ ነው።

፬· "ወረዳ" ማለት በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ህገ መንግስት አንቀጽ——— መሰረት የተደራጀ ከቀበሌ በላይና ከክልል መስተዳድር በታች የሆነ ደረጃ / እርከን/ ነው።

፭· "ቀበሌ" ማለት በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ህገ መንግስት አንቀጽ ——— መሰረት የተደራጀ ዝቅተኛ / ታችኛው/ የመስተዳድር ደረጃ/እርከን/ ነው።

፮· "ምክር ቤት" ወይም "የምክር ቤት አባል" ማለት እንደቅደም ተከተላቸው በአፋር ብሔራዊ ክልል ተቋቁመው የሚገኙ የክልል፣ የወረዳና የቀበሌ ምክር ቤቶች ወይም የም/ቤት አባላት ማለት ነው።

## ክፍል ሦስት

### መብቶችና ግዴታዎች

### አንቀጽ ሦስት

*መሰረታዊ መብቶች፣*

፩· በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ግዛት ውስጥ የሚኖር ማንኛውም ዜጋ ህግ በሚፈቅደው መሰረት በአፋር ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት የሚወከል ተመራጭ የመምረጥ መብት አለው።

፪· በአፋር ብሔራዊ ክልል የሚኖር ማንኛውም ዜጋ ከሌሎች ጋር በመሆን መርጦ የወከለውን ተወካይ በፈለገው ጊዜ መመርመር ፣ መገምገም፣ መመዘን ይችላል።

፫· በአፋር ብሔራዊ ክልል የሚኖር ማንኛውም ዜጋ መርጦ ለወከለው ተወካይ ሲሰጠው የቆየውን ድጋፍ የመሰረዝ፣ የማቋረጥ፣ ወይም የመቀጠል መብት አለው።

፬· ማንኛውም የህዝብ ተመራጭ (የምክር ቤት አባል) በመራጮቹ የሚቀርብለትን ምስጋና ፣ ተግሳፅ/እርማት/ ግምገማ ወይም ሂስ በግልፅና በአደባባይ የማሰራጨት፣ የመቃወምና የመንቀፍ መብት አለው።

### አንቀጽ አራት

### የህዝብ አመኔታ የሚለካበት አግባብ

አንድ የህዝብ ተወካይ /ተመራጭ/ የህዝብ አመኔታ የለውም ሊባል የሚችለው፦

፩· ተወካይ በተወከለበት የምርጫ አካባቢ የሚገኙት መራጮች ከግማሽ በላይ የሚሆኑ ምርጫ ባወጣው ደንብ መሰረት እንዲወርድላቸው ለምርጫ ቦርድ ጥያቄ ሲያቀርቡ፣

## PART TWO

### Article 2.

2. *Definitions*

Unless the context requires otherwise, in this Proclamation:

1/ "Deputy" means a member of the Council who has been elected to represent a certain constituency area and has obtained a certificate from the Electoral Board pursuant to implementation of law of Ethiopian Electoral Board;

2/ "Constituency" means, in accordance with electoral law, an area of special election area made up of specific number of inhabitants;

3/ "Elector" means an individual who has attained the age of 18 and resided in the area for more than two years in accordance with electoral law;

4/ "Woreda" means in accordance with Article.... of the Constitution of the Afar National Regional State, an organized district at levels higher than kebele and lower than regional Administration;

5/ "Kebele" means in accordance with Article... of the Constitution of the Afar National Regional State, an organized lowest level of administration;

6/ "Council" or Member of the Council" means regional, woreda and kebele councils organized in Afar National Region and members of the Councils, respectively.

## PART THREE

### *RIGHTS AND OBLIGATIONS*

### Article 3.

*Fundamental Rights*

1/ Any citizen who resides in the Afar National Regional State shall have the right to elect a deputy to represent the National Regional State of Afar based on law.

2/ Any citizen who resides in the Afar National Regional State may, together with others, investigate, evaluate and assess the representative he has elected at any time.

3/ Any citizen respiding in the Afar National Regional State has the right to cancel, terminate or continue his support of the representative he has elected.

4/ Any deputy has the right to publicly and openly resound the acclaim he/she receives from the electorate as well as to, similarly, refuse or counter reprimands, adrverse evaluations or criticisms made against him/her.

### Article 4.

*Standards of the Public Trust*

A Deputy/representative may lose his mandate of representation upon loss of trust by the electorate where:

1/ in accordance with the regulations of the Electoral Board, more than one-half of the electors requests the Electoral Board for removal;

፪· ከዚህ በላይ በንዑስ ቁጥር ፩ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ተወካዩ በተወከለበት የምርጫ አካባቢ ከሚገኙ መራጮች ማመልከቻ ሲቀርብና ምርጫ ቦርድ ባወጣው ደንብ መሰረት ም/ቤቱ በ፪/፫ኛ ድምፅ ውሣኔ ያስተላለፈ እንደሆነ፣ ወይም ደግሞ የክልሉ ምክር ቤት የህዝብ ውክልና ኃላፊነት ያጓደለ ተወካይ ጉዳዩ በ፪/፫ኛ ድምፅ ወስኖ ተወካዩ በተወከለበት የምርጫ አካባቢ ለሚገኙ መራጮች አቅርቦ ከግማሽ በላይ የሚሆኑ የምርጫ ቦርድ ባወጣው ደንብ መሠረት ተወካዩ እንዲወርድላቸው ሲጠይቁ የሚፈፀም ይሆናል።

፫· የልዩ ምርጫ አካባቢ ተወካይ የሚመለከት ከሆነ በምርጫ ቦርድ ህግ መሰረት ተወካዩን የመረጠው ህዝብ በተወካዩ ላይ አመኔታ ማጣቱ ሲረጋገጥ።

፬· በየደረጃው ያለው ምክር ቤት ተወካዩ ባሣየው የስነ–ምግባር ጉድለት የወከለውን ህዝብ በብቃት ሊወክለው አይችልም ብሎ በሁለት ሦስተኛ ድምፅ የወሰነ እንደሆነ ነው።

<u>አንቀጽ አምስት፣</u>

<u>የስነ–ምግባር መመዘኛዎች</u>

አንድ የምክር ቤት አባል በስነ–ምግባር ጉድለት እርምጃ ሊወሰድበት የሚችለው ቀጥለው ከተዘረዘሩት የስነ– ምግባር ጉድለቶች ቢያንስ አንዱን ወይም ከአንድ በላይ ፈፅሞ ሲገኝ ነው።

፩· ጉቦ መቀበል፣

፪· በወገን /በዘመድ/ በጎሳ፣ በአካባቢያዊነት ሲሰራ፣

፫· የህዝብና የመንግስት ገንዘብና ንብረት ለግል ጥቅም ሲያውል፣

፬· በሀይማኖት ፣ በዘር፣ በአካባቢያዊነት ፣ በጎሳ ሆን ብሎ ህዝብ ሲከፋፍል

፭· በህብረተሰቡ አስነዋሪ ተብለው የሚታወቁ ስነ–ምግባ ሮችን ፈፅሞ ሲገኝ፣

፮· ሆን ብሎ ለመንግስትና ለህዝብ የሚጎዱ ትላልቅ ወንጀ ሎችን ሲፈፅም፣

<u>አንቀጽ ስድስት</u>

<u>ስለሚወሰዱ እርምጃዎች፣</u>

፩· ምክር ቤቱ በሚያቋቁመው ኮሚቴ አማካይነት በስነ–ምግባር ብልሹነት የተከሰሰ ተወካይ ጉዳዩ ይጣራል።

፪· የምክር ቤቱ አጣሪ ኮሚቴ የሰጠው ውሣኔ መሰረት በማድረግ ከተወያየ በኋላ ይወስናል።

፫· ምክር ቤቱ እርምጃ መውሰድ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ተወካዩ ላይ የሚከተሉትን እርምጃዎች ሊወስድ ይችላል።

ሀ/ ለህዝብ ግልፅ በሆነ መንገድ ማስጠንቀቂያ ፣ ተግሣፅ ወይም ሂስ መስጠት፣

ለ/ ለተወሰነ ጊዜ ከምክር ቤቱ ማገድ፣

ሐ/ የስነ–ምግባር ብልሹነት አለው ተብሎ የታመነበት አባል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) /ሀ/ እና /ለ/ የተደነገጉትን ቅጣቶች ከተቀበለ በኋላ የስነ–ምግባር ብልሹነቱን የሚቀጥልበት ከሆነ በሁለት ሶስተኛ የምክር ቤቱ ድምፅ ከአባልነቱ ይሰረዛል፡–

መ/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፫/“ሀ” እስከ “ሐ” የተመለከቱት ቅጣቶች ቅደምተከተላቸውን ሣይጠብቁ ሊፈፀሙ ይችላሉ።



2/ and without prejudice to Sub-Article (1) of this Article, based on the electors application and the Electoral Board Regulations two-thirds of the Wereda Council approves the application by avote; or if he is a member of the kebele Council the electors application is submitted to the Electoral Board pursuant to the Regulations and the Kebele Council approves by two-third vote;

